# ፀረ-ሙስና

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ቅፅ 01 ቁጥር 22 ሚያዚያ 30 /2016/ ዓ.ም

## በኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) የተመራ ልዑክ ቡድን ከአለምዓቀፍ የብሪክስ የፀረ-ሙስና ቡድን ጋር ውይይት አደረገ

**የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድኑ በሶስት ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ ለአባል ሀገራት ያላትን አቋምና ተሞክሮ አንፀባርቃለች።**





በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) የተመራ ልዑክ ቡድን ከአለምዓቀፍ የብሪክስ የፀረ-ሙስና ቡድን ጋር በሩሲያ ሞስኮ ከተማ ውይይት አካሄደ። የውይይት መድረኩ ለሁለት ቀናት የተካሄደ ሲሆን፣ በፀረ-ሙስና ትብብር ዙሪያ ትኩረት ያደረገ መሆኑ ተገልጿል። የብሪክስ የጋራ አቋም ሰነድ የፀረ-ሙስና ትብብርና ንብረት መልሶ ማግኘት ውጤታማነትን በማሻሻል በብሪክስ የፀረ-ሙስና ስራ ቡድን (ACWG) ተዘጋጅቶ እንዲፀድቅ ለማድረግ በሰነዱ ላይ አስተያየት ተሰጥቷል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድኑ በሶስት ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ ለአባል ሀገራት ያላትን



ወደ ገጽ 5 ዞሯል..

## በውስጥ ገፆች

- የትራፊክ ፖሊሶች ህብረተሰቡን በታማኝነት፣ በፍትሃዊነትና በሙያዊ ብቃት በማገልገል ሙስናን ሊፀየፉ
ገጽ 2
- የኖክ ነዳጅ ማደያ ስራ አስኪያጅን በማስፈራራት ገንዘብ የተቀበሉ በእስራትና በገንዘብ ተቀጡ
ገጽ 6

## የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ከሀገር የሸሹ ሀብቶችን ለማስመለስ በጋራ መስራት እንዳለባቸው ተገለፀ።

**15ኛው የምስራቅ አፍሪካ አገሮች የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ማህበር ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ (15th EAAACA Annual General Meeting) በአዲስ አበባ ተካሂዷል**

የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት በሙስና ከሀገር የሸሹ ሀብቶችን ለማስመለስና ግልፅነት የሰፈነበት አሰራርን ለመተግበር ትብብርን ማጎልበት እንደሚገባ የምስራቅ አፍሪካ የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ማህበር ፕሬዚዳንት ኒሪሪ ማዲሊ ገለጹ። የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ማህበር የተመዘበሩና ከሀገር የሸሹ ሃብቶችን በቅንጅት ማስመለስ ላይ ያተኮረ ጉባኤ በአዲስ አበባ አካሂዷል።

በመድረኩ ኢትዮጵያን ጨምሮ ስምንት የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የፀረ-ሙስና ኮሚሽነሮች፣ የስራ ዘርፍ ኃላፊዎችና ተወካዮች ተገኝተዋል። በውይይቱ በሙስና የሚሸሹና የሚመዘበሩ ሀብቶችን ለማስመለስ በትብብር መስራት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ ተነስቷል።



ወደ ገጽ 3 ዞሯል..




## በሥነምግባር የታነጸ ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዳ ዜጋ ለማፍራት ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት አሳሰበ

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በወላይታ ሶዶ ከተማ ውይይት አካሂዷል፡፡





በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ዋና አፈ ጉባኤ ወ/ሮ ፀሐይ ወራሳ ሙስና በሀገር ልማት ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ ይገኛል ብለዋል፡፡ በመሆኑም በሥነምግባር የታነፀ ከብልሹ አሰራር እና ከሙስና የፀዳ ዜጋ ለማፍራት ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ ማሳሰባቸውን ተዘግቧል፡፡ በክልሉ ሙስናን በመከላከል ረገድ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ቢሆንም ተግባሩን ለመቀነስ ገና ብዙ ትግል ስለሚጠይቅ ጥንካሬዎችንና ጉድለቶችን ለመለየት ያለመ መድረክ መዘጋጀቱን ተናግረዋል፡፡

## የትራፊክ ፖሊሶች ህብረተሰቡን በታማኝነት፣ በፍትሃዊነትና በሙያዊ ብቃት በማገልገል ሙስናን ሊፀየፉ ይገባል





የትራፊክ ፖሊሶች ህብረተሰቡን በታማኝነት፣ በፍትሃዊነትና በሙያዊ ብቃት በማገልገል ሙስናን ሊፀየፉ እንደሚገባ ተገልጿል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለቂርቆስ ክ/ከተማ ትራፊክ ፖሊስ አባላት በሙያዊ ሥነምግባርና ሙስና መከላከል ዙሪያ ስልጠና ሰጥቷል፡፡

በስልጠናው ንግግር ያደረጉት የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር አቶ አሰፋ ቶላ እንደገለፁት የትራፊክ ፖሊሶች ህብረተሰቡን በታማኝነት፣ በፍትሃዊነትና በሙያዊ ብቃት በማገልገል ሙስናን ሊፀየፉ ይገባል ብለዋል፡፡ የትራፊክ ፖሊሶች ህግን በተሟላ ሁኔታ በማክበርና በማስከበር የህዝብ አመኔታን በመፍጠር ሙስናን የመከላከል ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባም ም/ኮምሽነሩ ጠቅሰዋል፡፡ ም/ኮሚሽነሩ አክለውም የትራፊክ ፖሊሶች የመንገድና የህብረተሰቡን ደህንነት በመጠበቅ ሂደት ተግባራቸውና ውሳኔያቸው ከአድልዎ የፀዳና ግልፅኝነት ያለው መሆን እንዳለበት ተናግረዋል፡፡ የቂርቆስ ክ/ከተማ ትራፊክ ፖሊስ ኃላፊ ኢ/ር ያደሳ ሚደቅሳ በበኩላቸው ትራፊክ ፖሊስ የህዝብንና የመንገድን ደህንነት ከመጠበቅ አኳያ ሚናችን ከፍተኛ በመሆኑ በከተማችን የሚደረጉ ሁነቶችን በብቃትና በታማኝነት መፈፀም አለብን ብለዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ የሞተር አጀብ ዋና ኢንስፔክተር ሰላሙ ከርቲሶ ስልጠናው ስራዎቻችንን ስናከናውን ሙያዊ ሥነምግባር በተላበሰ መልኩ ለማከናወን የሚያግዝ መሆኑን ገልፀው፣ በቀጣይም በሌሎች ክ/ከተሞች መስፋት እንዳለበት መናገራቸውን ከኮሚሽኑ የፌስቡክ ገፅ የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡ በኮሚሽኑ የስልጠና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ጀንበሩ ኢርኮ ስልጠናውን በሰጡበት ወቅት እንደተናገሩት የትራፊክ ፖሊስ አባላት ተግባሮቻቸውን ሲያከናውኑ ሙያዊ ሥነምግባርን ባከበረ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡





## ከገጽ አንድ የዞረ…

ሙስና በአፍሪካ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ዘርፎች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እያሳረፈ በመሆኑ ሀገራት ይህንን ለመከላከል በጋራ መቆም እንዳለባቸውም ተመላክቷል:: የምስራቅ አፍሪካ የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ማህበር ፕሬዚዳንት ኒሪሪ ማዲሲ በዚሁ ወቅት እንደገለጹት፣ ሙስናን በቋሚነት ለመከላከልና ለመዋጋት አንድ ሀገር ብቻውን ውጤታማ ሊሆን አይችልም ብለዋል:: ማህበሩ በተሰጠው ሃላፊነት መሰረት በሀገራቱ መካከል ተመዝብረው የሚዘዋወሩ ሀብቶችን ለማስመለስ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን አሰራርን ለማጠናከርና ሙስናን ለመከላከል ትብብርን ማጎልበት ወሳኝ ነው ብለዋል::

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) በበኩላቸው ኢትዮጵያን ጨምሮ በማህበሩ ውስጥ ያሉ ሀገራት ሙስናን ለመታገል ቅንጅታዊ አሰራር መከተላቸው የግድ መሆኑን ጠቅሰዋል::

በሀገራቱ መካከል የሚስተዋለውን የሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለማስቀረት የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪካ ህብረት የፀረ-ሙስና ስምምነቶችን ትግበራ ማጠናከር ላይ ትኩረት እንደሚደረግም ገልጸዋል::

መድረኩ በሀገራቱ መካከል በሙስና የሀብት ማሸሽና መመዝበርን ጨምሮ የሚስተዋሉ ህገ-ወጥ ተግባራትን ለመቀልበስ መግባባት የተፈጠረበት መሆኑን ተናግረዋል:: በዚህም በሀገራቱ መካከል መረጃን በመለዋወጥና በቅንጅት በመስራት ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል አመላክተዋል:: ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት ዓመታት ማህበሩን በምክትል ፕሬዝዳንትነት የመራች ሲሆን፥ በመድረኩ በፀረ-ሙስና ትግሉ የጀመረቻቸውን ስራዎችና ያላትን ልምድ አካፍላለች:: ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ታንዛንያ፣ ሩዋንዳ፣ ጅቡቲ፣ ኡጋንዳ፣ ቡሩንዲና ደቡብ ሱዳን የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ማህበር አባል ሀገራት ናቸው::



ጋዜጣዊ መግለጫ

PRESS RELEASE

በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ከምዝበራ የዳነ የመንግስት ንብረት እና ገንዘብ

በ2016 በጀት አመት በ9 ወራት በፌደራል፣ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የሙስና ወንጀል ድርጊት ከመፈጸሙ በፊት በተሰራ የአስቸኳይ የሙስና መከላከል 1 ቢሊየን ብር በላይ የመንግስት ሀብትና ንብረት ከምዝበራ ማዳን የተቻለ ሲሆን በዝርዝር እንደሚከተለው ተመላክቷል።

| ተ.ቁ | በፌ/ሪ/ክልል/ከተማ አስተዳደር | ከሙስና የዳነ ጥሬ ገንዘብ | ከሙስና የዳነ መሬት በካ.ሜ | ከሙስና የዳነ ንብረት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የፌደራል ተቋማት | 678,730,266.99 | - | - |
| 2 | ኦሮሚያ | 2,952,687.68 | 105,070 | - |
| 3 | አማራ | 1,493,160.00 | 4,771 | [illegible] |
| 4 | ደቡብ ኢትዮጵያ | - | - | - |
| 5 | ሲዳማ | 10,309,906.43 | 8,280 | [illegible] |
| 6 | ሐረር | - | - | - |
| 7 | ሶማሌ | 8,867,632.00 | 6,513 | [illegible] |
| 8 | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 226,860,403.86 | - | - |
| 9 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 22,674,439.39 | 200 | [illegible] |
| 10 | ጋምቤላ | 218,827.80 | - | - |
| 11 | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | 17,287,315.85 | 22,160,266.7 | [illegible] |
| 12 | ትግራይ | - | - | - |
| 13 | አፋር | 7,602,141.00 | - | [illegible] |
| 14 | ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር | 56,000,000.00 | - | [illegible] |
| 15 | አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር | 962,771,856.62 | 10,282 | 2 ላፕቶፕ |
| | ድምር | 1,999,089,528.42 | 22,303,482.7 | [illegible] |

ስልክ TEL 011552-77-84 011552-77-86 011558-09-48 | ፖ.ሳ.ቁ P.O.Box 34798/99 ኢ-ሜይል E-mail FeaccEthiopia2013@et | ፋክስ/Fax 011553-69-02 ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial | አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa, Ethiopia



ጋዜጣዊ መግለጫ

PRESS RELEASE

በፌደራል በ25ቱም ዘርፎች ውስጥ ሊፈፀሙ የታሰቡ የሙስና ወንጀል ወደ ድርጊት ከመለወጣቸው በፊት በተሰራ 76 የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ ብር 678,730,266.98 እና 8,490 የአሜሪካን ዶላር የሆነ ገንዘብ ከሙስና ምዝበራ ማዳን ተችሏል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ በፌደራል፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች በተሰራ 373 የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ በጥሬ ገንዘብ ብር 1,999,089,528.42 (አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሚሊዮን ሰማንያ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከአርባ ሁለት ሳንቲም) እና መጠኑ 22,303,482.7 ካሬ ሜትር የሆነ የከተማ እና የገጠር ቦታ ከሙስና ምዝበራ ማዳን ተችሏል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከምዝበራው ጋር ግንኙነት ያላቸውን አካላት ተጠያቂ ለማድረግ እየተሰራ ሲሆን ህብረተሰቡ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን በመስጠት ረገድ የነበረው ሚና የሚመሰገን በመሆኑ በቀጣይም በፀረ-ሙስና ትግሉ ላይ ንቁ ተሳትፎ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

ከሙስና የፀዳች እና የበለፀገች ኢትዮጵያን እውን እናድርግ !

ስልክ TEL 011552-77-84 011552-77-86 011558-09-48 | ፖ.ሳ.ቁ P.O.Box 34798/99 ኢ-ሜይል E-mail FeaccEthiopia2013@et | ፋክስ/Fax 011553-69-02 ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial | አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa, Ethiopia

# የሚዲያ ተቋማት ከፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር ያላቸውን ግንኙነት ሊያጠናክሩ ይገባል - ቋሚ ኮሚቴው





ሚዲያዎች ከዴሞክራሲ ተቋማት ጋር በቅርበት በመስራት የህዝብ ድምፅ መሆን እንደሚገባቸው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አመላክቷል:: በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት እና በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት የአዳማ ቅርንጫፎች የመስክ ምልከታ ተደርጎባቸዋል:: የሚዲያ ተቋማቱ ኹነቶችን ከመዘገብ በተጨማሪ የህዝቡን ዴሞክራሲያዊና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች በሚመልሱ የይዘት ሥራዎች ላይ እንዲያተኩሩ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ እውነቱ አለነ አመላክተዋል:: የሚዲያ ተቋማት እንደ የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም እና ምርጫ ቦርድ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ሊያጠናክሩ ይገባል ብለዋል:: አክለውም የማህበረሰቡን አንገብጋቢ ጥያቄዎች ለመመለስ የሚረዱ ዘገባዎች ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ ማመልከታቸውን የተገኘው መረጃ ያመለክታል::

# በሀሰት ሰነድ የመንግስት ይዞታ ላይ ካርታ የሰጡና ይዞታውን የሸጡ እስከ 13 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ተቀጡ

ሀሰተኛ ሰነዶችን በመጠቀም በተጭበረበረ መንገድ 638 ካሬ ሜትር የመንግስት ይዞታ ላይ የማረጋገጫ ካርታ የሰጡና ይዞታውን ወስደው በመሸጥ ጉዳት እንዲደርስ አድርገዋል ተብለው ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም ከባድ የሙስና ወንጀል የተከሰሱ ግለሰቦች በጽኑ እስራትና በገንዘብ እንዲቀጡ ተወስኗል::

የግራ ቀኝ የሰነድና የሰው ማስረጃዎችን መርምሮ የቅጣት ውሳኔ የወሰነው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 5ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው:: በዛሬው ቀጠሮ በጽኑ እስራትና በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ የተወሰነባቸው ተከሳሾች ቀደም ሲል ሳምራዊት ኪዳኔ ሀጎስ የተባለ መጠሪያ ስሟን ወደ ሲፈን አበራ የቀየረችው 1ኛ ተከሳሽ እንዲሁም ለምለም ኪዳኔ ሀጎስ የነበረውን ስሟን ወደ ሀቂ ዶሮ ገመቹ በመቀየር የነዋሪነት መታወቂያ አውጥታለች የተባለችው 2ኛ ተከሳሽ ሀቂ ዶሮ ገመቹ ፣ 3ኛ ይርገዶ ሙሉጌታ፣ 4ኛ ተከሳሽ ሀብታሙ አበራ ፣ በአሁን ወቅት በጡረታ የተገለለው የቀድሞ የቦሌ ክ/ከተማ የመሬት ልማት ይዞታ አስተዳደር ይዞታ አጣሪ ባለሙያ መለስ አብጤ፣ ቴክኒክ አጣሪ ባለሙያ ቢኒያም ወንደሰን እና በግል ስራ ይተዳደራሉ የተባሉት ኦሊያድ በቀለና አሳምነው ተስፋዬ ናቸው::

ከእነዚህ ተከሳሾች ጋር ክስ ቀርቦበት የነበረው 7ኛ ተከሳሽ ማለትም የቦሌ ክ/ከተማ የሰነድ አልባ ዝግጅት ኃላፊ የነበረው በሃይሉ አባተን በሚመለከት ዘግይቶ በመቅረቡ ምክንያት ጉዳዩ ተነጥሏል::

የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ-ህግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 1 ሀ እና ለ፣ አንቀጽ 33 እና የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/1 ሀ፣ ንዑስ ቁጥር 2 ስር የተመላከተውን ድንጋጌ እና የታክስ አስተዳደር አዋጁን ተላልፈዋል በማለት የተከሳሾቹን የተሳትፎ ደረጃ ጠቅሶ ዝርዝር ክስ አቅርቦባቸው ነበር::

በዚህም ባቀረበው በአንደኛው ክስ ዝርዝሩ ላይ እንደተመላከተው ተከሳሾቹ በጥቅም በመመሳጠር ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ በቀድሞ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ስር የሚገኙ ይዞታዎችን ከ1ኛ እስከ 4ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች በሀሰተኛ ሰነድ የአርሶ አደር ልጅ ነን በማለት ሀሰተኛ የነዋሪነት መታወቂያ እና የአርሶ አደር ኮሚቴ ቃለ ጉባዔ ሀሰተኛ ሰነዶችን በክፍለ ከተማው ይሰሩ ለነበሩት ከ5ኛ እስከ 7ኛ ተራ ቁጥር ለተጠቀሱ ተከሳሾች በማቅረብ የይዞታ ካርታ እንዲዘጋጅላቸው ማድረግ እና በተጭበረበረ መንገድ የወሰዱትን 638 ካሬ ሜትር ይዞታን ደግሞ ሸጠው በመንግስት ላይ ጉዳት እንዲደርስ አድርገዋል ተብለው በደረጃው የተከሰሱ ግለሰቦች ናቸው::

በዚህ መልኩ በተጭበረበረ መንገድ በ1ኛ ተከሳሽ ስም 112 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ ካርታ ተሰርቶ የመንግስት ባዶ መሬት መሰጠቱ የተገለጸ ሲሆን ÷ በ2ኛ ተከሳሽ ስም 200 ካሬ ሜትር ፣ በ3ኛ ተከሳሽ 326 ካሬ ሜትር እንዲሁም በ4ኛ ተከሳሽ ስም 500 ካሬ ሜትር የመንግስት ቦታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲወስዱ መደረጉ ተጠቅሷል:: በተጭበረበረ መንገድ ከተወሰዱ ይዞታዎች ውስጥ 1ኛ ተከሳሽ በራሷ ስም የወሰደችውን ይዞታ እንዲሁም በ2ኛ እና በ3ኛ ተከሳሾች ስም የተወሰዱ ይዞታዎችን ውክልና በመውሰድ በ8ኛ እና በ9ኛ ተከሳሾች አግባቢነትና አሻሻጭነት ለሁለት ግለሰቦች መሸጣቸውም ጠቅሶ ዐቃቤ-ህግ በክሱ ላይ አስፍሯል::

ፍርድ ቤቱ በሁለተኛው ክስ ማለትም ሀሰተኛ ሰነዶችን አዘጋጅተው አቅርበዋል ተብለው የተከሰሱ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ በሃሰተኛ ሰነድ የተፈጸመ የወንጀል ድርጊት መሆኑን በአንደኛው ክስ መገለጹን ጠቅሶ ÷ ሁለተኛው ክስ በአንደኛው ክስ እንዲጠቃለል ብይን ሰጥቷል።

በ3ኛ ክስ ደግሞ በ8ኛ እና በ9ኛ ተከሳሾች ላይ ተከሳሾቹ የይዞታውን ህጋዊነት ደብቀው ገዢዎችን በማግባባት ይዞታው ተሸጦ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር ጥቅም ያገኙ ሲሆን ÷ 1ኛ ተከሳሽ የገንዘቡን ምንጭ ለመደበቅ ጃፓን ስሪት ቲዮታ ሞዴል የቤት መኪና መግዛቷ ተጠቅሶ ÷ በወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል ተከሰዋል::

በ4ኛው ክስ ደግሞ 1ኛ ተከሳሽ አንደኛውን ይዞታ በ7 ሚሊየን 700 ሺህ ብር፣ ሌላኛውን ይዞታ ደግሞ በ17 ሚሊየን ብር ለዐቃቤ-ህግ ለ15ኛ እና ለ16 ኛ ምስክሮች ለሆኑ ግለሰቦች ከሸጠች በኋላ የሰነዱን ትክክለኛ ባህሪ በመደበቅ እያንዳንዳቸውን ይዞታዎች በ1 ሚሊየን ብር ብቻ እንደሸጠች በማድረግ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 123 ንዑስ ቁጥር 1ለ ስር የተመላከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የቴን ብር ቀረጥ ክፍያን መሰወር ወንጀል ክስ ቀርቦባት ነበር:: ክሱ ከቀረበባቸው ተከሳሾች መካከል 2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ችሎት ባለመቅረባቸው ጉዳያቸው በሌሉበት ነው የታየው::

ሌሎቹ 1ኛ፣ 5ኛ፣ 6ኛ፣ 8ኛ እና 9ኛ ተከሳሾች ግን ክሱ ከደረሳቸው በኋላ የተከሰሱበት ድንጋጌ ዋስትና የማያሰጥ መሆኑን ተከትሎ በማረሚያ ቤት ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ተደርጓል:: ከዚህም በኋላ ተከሳሾቹ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸማቸውን ጠቅሰው የሰጡትን የዕምነት ክህደት ቃል ተከትሎ ዐቃቤ-ህግ 18 የሰው ምስክሮችንና ገላጭና አስረጂ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል::

ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ-ህግ ማስረጃን መርምሮ ተከሳሾቹ እንዲከላከሉ ብይን የሰጠ ቢሆንም ተከሳሾቹ በተለያዩ ቀናት ባቀረቡት የተናጠልና የጣምራ መከላከያ ማስረጃዎች ግን የዐቃቤ-ህግ ማስረጃን በተገቢው ማስተባበል ባለመቻላቸው የጥፋተኝነት ፍርድ የተላለፈባቸው ሲሆን ÷ 2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች በሌሉበት ጥፋተኛ ተብለዋል::

ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ-ህግ ተከሳሾች ላይ ያቀረበውን የቅጣት ማክበጃ አስተያየትና ችሎት የቀረቡ አምስቱ ተከሳሾች ያቀረቡትን የቅጣት ማቅለያ አስተያየት መርምሮ ዛሬ የቅጣት ውሳኔ አስተላልፏል::

ወደ ገጽ 5 ዞሯል...





ከገጽ 1 የዞረ…

አቋምና ተሞክሮ አንፀባርቃለች፡፡ እነዚህም (ሀ) ሥነ-ምግባርና ግንባታ ፣ (ለ) የሙስና መከላከል ተግባራት (ሐ) ዓለም አቀፍ ትብብርና ሕግ አስከባሪነት ትኩረት ያደረገ ገለጻ ተደርጓል፡፡

የBRICS አገሮች በባዕድ አገሮች ውስጥ የተከማቸው የተከለከሉ የገንዘብ ዝውውሮችና ተገቢ ያልሆነ ሀብት በኢኮኖሚና ዘላቂ እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ዓለም አቀፋዊ ተፈታታኝ ሁኔታ መሆናቸውን በተደጋጋሚ አምነዋል፡፡ በንብረት ማገገም ረገድ የተሻለ ትብብር ማግኘት ለረጅም ጊዜ ቅድሚያ የሚሰጠውም ለዚሁ ነው፡፡ ባለፉት ዓመታት ብሪክስ በዚህ ረገድ በርካታ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡

ከእነዚህም መካከል እኤአ በ2019 የንብረት ማገገምን አስመልክቶ የተከናወነ ስብሰባ፣ በ2022 ለሙስና አስተማማኝ መጠለያ አለመቀበልን በተመለከተ የተጀመረውን ተነሳሽነትና በ2023 የንብረት ማገገምን አስመልክቶ የብሪክስ መረብ ማቋቋም ይገኙበታል፡፡ አገሮች በአካባቢው እድገት ቢያሳዩም አሁንም ቢሆን መሻሻልና የጠበቀ ግንኙነትን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች አንዳሉ በዉይይቱ ለመለየት ተችሏል፡፡

ከዚህም በላይ አንዳንድ ግምቶች እንደሚያሳዩት ከወንጀል ትርፍ ውስጥ 1 በመቶ ውስጡን ብቻ በማግኘት ንብረቶችን መልሶ ማግኘት ቀጣይነት ያለው ፈተና ሆኖ በአባል ሀገራት ቀጥሏል፡፡

ይህም አሁን ያሉትን የአሰራር ስርዓቶች በቂ ውጤት የሌላቸው መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም ህገ ወጥ ንብረት ንዋያትን በመለየት፣ በማደናቀፍ፣ በመከላከልና በመታገል ረገድ አባል ሀገራትን ለማገዝ ጠንካራ የአሰራር መሳሪያዎች ያስፈልጋሉ፡፡

ከገጽ 4 የዞረ…

በዚህም ቀደም ሲል ሳምራዊት ኪዳኔ ሀጎስ የተባለ መጠሪያ ስሟን ወደ ሲፈን አበራ ቀይራ የነዋሪነት መታወቂያ አውጥታለች የተባለችው 1ኛ ተከሳሽን ያቀረበችው የቅጣት ማቅለያ አስተያየት ተይዞላት በእርከን 30 መሰረት በ13 ዓመት ጽኑ እስራት እና በ5 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንድትቀጣ ወስኗል፡፡

2ኛ ተከሳሽ በ2 ዓመት ከ9 ወር ጽኑ አስራትና በ4 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ የተቀጣች ሲሆን ፥ 3ኛ ተከሳሽ ደግሞ በ4 ዓመት ጽኑ እስራትና በ71 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ ፣ 5ኛ ተከሳሽ 4 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራትና በ4 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ ፣ 6ኛ ተከሳሽ በ5 ዓመት ጽኑ እስራትና በ2 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ ፣ 8ኛ እና 9ኛ ተከሳሾች ደግሞ እያንዳንዳቸው በ12 ዓመት ጽኑ እስራትና በ3 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ተወ ስኗል፡፡

ፖሊስ ያልተያዙ ሦስት ተከሳሾ ችን አፈላልጎ የተጣለባቸውን ቅጣት እንዲፈጽሙ ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲያስረክብ ታዟል፡፡

## የነዋሪዎች ቅሬታ ምንጭ የሆኑትን ቀልጣፋና ከተማዋን የሚመጥን የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ሌብነት እና ጉቦኝነት ላይ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት የምንሰራ ይሆናል - ከንቲባ አዳነች አቤቤ





የነዋሪዎች ቅሬታ ምንጭ የሆኑትን ቀልጣፋና ከተማዋን የሚመጥን የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ሌብነት እና ጉቦኝነት ላይ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት እንደሚሰሩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገልፀዋል፡፡ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ እንደጠናቀቀ መግለፃቸውን ገልፀዋል፡፡

# በፍትህ ተቋማት የሚታዩ ውስንነቶችን በመቅረፍ የተፋጠነና ከሙስና የጸዳ አገልግሎት ለተገልጋዩ መስጠት እንደሚገባ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት አስታወቀ



በፍትህ ተቋማት የሚታዩ ውስንነቶችን በመቅረፍ የተፋጠነና ከሙስና የጸዳ አገልግሎት ለተገልጋዩ መስጠት እንደሚገባ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት አስታውቋል። የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የፍርድ ቤቶችና የፍትህ ተቋማት ሪፎርም የስትሪንግ ኮሚቴ የውይይት መድረክ በአርባምንጭ ከተማ ተከናውኗል። የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ዋና አፈ ጉባኤና የክልሉ የፍርድ ቤቶችና የፍትህ ተቋማት ትራንስፎርሜሽን የስትሪንግ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወ/ሮ ፀሐይ ወራሳ እንደገለጹት በክልሉ በ6ቱ የዞን ማዕከላት በፍርድ ቤቶችና በፍትህ ተቋማት ረገድ ህዝባዊ መድረክ ተከናውኗል። ይህም በዘርፉ የሚታየውን ጉድለት ለማረምና ጥንካሬዎችን አጠናክሮ ለማስቀጠል እንዲሁም እንደ ክልል በተቋማቱ ረገድ ወደ ሪፎርም ለመግባት እንደሚያግዝ ሰብሳቢዋ አንስተዋል።



ሰብሳቢዋ አክለውም ንቅናቄው በሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች በፍትህ ረገድ ከህዝቡ የተነሱና መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ ውስንነቶችን ለማረም የሚያግዝ ነው ብለዋል። በአንዳንድ ፍርድ ቤቶች ጉቦ በመቀበል ፍትህን የሚያዛቡ እንዳሉ በ6ቱ የክልል ማዕከላት

የውይይት መድረኩን የመሩት የክልሉ ም/ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ወ/ሮ ወላይቴ ቢቶን ጨምሮ ሌሎች አወያዮች በየመድረኩ መነሳቱን ጠቅሰዋል። የትራፊክ ፖሊሶች ከቁጥጥርና ክትትል ስራ ይልቅ ገንዘብ በማሳደድ ላይ ማተኮር በየማእከላቱ ከህዝቡ የተነሱ ጥያቄዎች እንደነበሩ በሪፖርት አቅራቢዎቹ ተጠቅሷል። በአጠቃላይ በፍ/ቤቶችና በፍትህ መዋቅሩ ረገድ የተሻሉ ጅምር ስራዎችን በማጠናከርና ችግሮችን ከመሠረቱ በመቅረፍ የፍትህ ስርዓቱን ቀልጣፋና ከእጅ መንሻ የጸዳ እንዲሆን የትኩረት አካል በማድረግ መፍትሄ ሊበጅለት እንደሚገባ በውይይት መድረኩ ቀርቧል። በውይይቱ ማጠቃለያ ወ/ሮ ጸሀይ ወራሳ እንደገለጹት በፍ/ቤቶችና በፍትህ ተቋማት ላይ በየማእከላቱ የተነሱት የህዝብ አስተያየቶች ምን ያህል ህዝባችን እየተጎዳ እንዳለና ፍትህን አቅምና ዘመድ ያለው ብቻ እያገኘ እንደሆነ ተገንዝበናል ብለዋል።

ከአቅም በላይ ገዝፎ የህዝባችንን ህልውና እየተፈታተነ ያለውን በፍትህ ሴክተሩ ረገድ እየታየ ያለውን ብልሹ አሰራርና ግድፈት ለማረም የስትሪንግ ኮሚቴው ክትትሉን እንደሚያጠናክርና ችግሮችን በመቅረፍ ረገድ የተሻለ ለውጥ እንደሚመጣ ይመጣል ብለዋል።

# የኖክ ነዳጅ ማደያ ስራ አስኪያጅን በማስፈራራት ገንዘብ የተቀበሉ በእስራትና በገንዘብ ተቀጡ



የኖክ ነዳጅ ማደያ ስራ አስኪያጅን በወንጀል ትፈለጋለህ በማለት አስፈራርተው ገንዘብ ተቀብለዋል ተብለው ስልጣንን ያለአግባብ መገልገል ሙስና ወንጀል የተከሰሱ አምስት ግለሰቦች እስከ 13 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና በገንዘብ እንዲቀጡ ተወሰነ። የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት የቅጣት ውሳኔ የወሰነባቸው ተከሳሾች 1ኛ ጫላ መገርሳ፣ ለሊሳ በቀለ፣ ዳዊት ጉደታ፣ ዮሃንስ ደረጄ እና ብርቱካን ለታ ናቸው። የክልሉ ፍትህ ቢሮ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ ተከሳሾቹ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 ንዑስ ቁጥር 1 ሀ ና ለ እንዲሁም የሙስና ወንጀልን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9 ንዑስ ቁጥር 2 ስር የተመላከተውን ድንጋጌ እና በአዋጅ ቁጥር 780/2005 አንቀጽ 29/1 ስር የተመላከተውን ድንጋጌ መተላለፋቸውን ጠቅሶ በ2015 ዓ.ም ክስ መስርቶባቸው ነበር።

በክሱ ዝርዝር ላይ እንደተመላከተው፤ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌሎች ለማስገኘት በማሰብ በመጋቢት 19 ቀን 2015 ዓ.ም ከቀኑ 11:00 ሰዓት ላይ በሸገር ከተማ ገፈርሳ ክፍለ ከተማ አካባቢ በሚገኝ የኖክ ነዳጅ ማደያ ስራ አስኪያጅ የሆነ የግል ተበዳይን የፀጥታ አካላት ነን፣ በወንጀል ትፈለጋለህ በማለት መንገድ ላይ በማስቆም ከውጭ ወደ ውስጥ እንዳይታይ አድርገው በስቲከር ሸፍነው ወደአዘጋጁት የቤት መኪና ውስጥ በማስገባት ወደ መልካ ናኖ ክ/ከ አንፎ ወደ ተባለ አካባቢ ወስደውታል። ከዚህም በኋላ የሞተ ሰው ፎቶ ለግል ተበዳዩ በማሳየትና በመሳሪያ በማስፈራራት ግማሽ ሚሊየን ብር እንዲያመጣና እንደሚለቁት በመግለጽ ገንዘቡን ካልከፈለ ደግሞ ወደ ጦር ኃይሎች እንወስድኃለን በማለት ገንዘብ እንዲከፍል መጠየቃቸውን ተከትሎ የግል ተበዳዩ በባንክ ሂሳቡ ውስጥ 100 ሺህ እንዳለው ገልጾ መልስ መስጠቱ በክሱ ተመላክቷል።

በዚህም ጊዜ 1ኛ ተከሳሽ ባለቤቱ በሆነችው በ5ኛ ተከሳሽ የባንክ ሂሳብ በሞባይል ባንኪንግ የግል ተበዳዩ 100 ሺህ ብር እንዲያዘዋውር ያደረገና ቀሪውን 400 ሺህ ብር እንዲያመጣ በማስጠንቀቅ የለቀቁት መሆኑን ዐቃቤ ሕግ በክሱ ላይ የጠቀሰ ሲሆን፤ በህገወጥ መንገድ የተገኘውን ገንዘብ ደግሞ 5ኛ ተከሳሽ ከአንደኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን ምንጩን ለመደበቅ በማሰብ በተለያዩ መጠኖች ወጪ በማድረግ ለግል ጥቅም ያዋሉት መሆኑ በክሱ ዝርዝር ላይ ሰፍሯል። ተከሳሾቹ ክሱ ከደረሳቸው በኋላ ድርጊቱን ክደው በመከራከራቸው ዐቃቤ ሕግ የሰው ምስክሮችን፣ አስረጂና ገላጭ የሰነድ ማስረጃዎችን ለችሎቱ አቅርቧል። ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን መርምሮ ተከሳሾቹ በተከሰሱበት ድንጋጌ እንዲከላከሉ ብይን ቢሰጥም ተከሳሾቹ በተገቢው መከላከል ባለመቻላቸው የጥፋተኝነት ፍርድ አስተላልፎባቸዋል።

ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግን ቅጣት ማክበጃ አስተያየትንና የተከሳሾቹ የቅጣት ማቅለያ አስተያየት በመያዝ 1ኛ ተከሳሽን በ13 ዓመት ጽኑ እስራትና በ3 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል። ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾችን ደግሞ እያንዳንዳቸውን በ7 ዓመት ጽኑ እስራትና በ3 ሺህ ብር የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ የወሰነው ፍርድ ቤቱ 5ኛ ተከሳሽን በሚመለከት በ1 ዓመት እስራትና በ1 ሺህ ብር ገንዘብ እንዲቀጡ ወስኗል።

# የሩሲያ ምክትል የመከላከያ ሚኒስትር ጉቦ በመቀበል ተጠርጥረው ታሰሩ



የሩሲያው መከላከያ ሚኒስትር ሰርጌ ሾይጉ ምክትሎች ከሆኑት አንዱ ጉቦ በመቀበል ተጠርጥረው መታሰራቸው ተገልጿል። ምክትል ሚኒስትሩ ፕሬዝደንት ፑቲን በዩክሬን ልዩ ያሉትን ወታደራዊ ዘመቻ ከከፈቱ ከየካቲት 2022 ወዲህ በሙስና ተጠርጥረው የታሰሩ ከፍተኛ ባለስልጣን መሆናቸውን ሮይተርስ ዘግቧል።

እንደዘገባው ከሆነ ምክትል የመከላከያ ሚኒስትሩ ቲሙር ኢቫኖቭ በቁጥጥር ስር የዋሉት ባለፈው ማክሰኞ ነው። ምክትል ሚኒስትሩ በተጠረጠሩበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ የ15 አመታት እስር ይጠብቃቸዋል። ፕሬዝደንት ፑቲን በዩክሬን ባለው ጦርነት ስራ ሰጥተዋቸው እየሰሩ የነበሩት የሾይጉ አጋር ድንገተኛ እስር፣ ሩሲያ ከሶቬት ህብረት መውደቅ በኋላ በጦሯ ውስጥ በተንሰራፋው ሙስና ላይ ልትዘምት ነው የሚል ጥርጣሬን ፈጥሯል።

ክሬሚሊን ፕሬዝደንት ፑቲን እና መከላከያ ሚኒስትሩ ሾይጉ የምክትል ሚኒስትሩ እስር ጉዳይ ተግሯቸዋል ብሏል። ኢቫኖቭ ከፍተኛ የመከላከያ ባለስጣናት ማክሰኞ እለት ባደረጉት ስብሰባ ላይ ተገኝተው እንደነበር አል ዓይን አማረኛ ዘግቧል። ከፈረንጆቹ 2016 ጀምሮ ምክትል ሚኒስትር ሆነው ሲያገለግሉ የቆዩት ኢቫኖቭ በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ ንብረት የማስተዳደር ኃላፊነት ነበራቸው።

ሮይተርስ የሩሲያውን ኮመርሳንት ጋዜጣ ጠቅሶ እንደዘገበዘው የ48ቱ ኢቫኖቭ በቁጥጥር ስር የዋሉት በሶቬት ጊዜ የነበረውን ኬጂቢን በተካው የሩሲያው ፌደራል ሴኩሪቲ ሰርቪስ(ኤፍኤስቢ) ነው። ፕሬዝደንት ፑቲን ባለፈው ወር ነበር በመከላከያ ሚኒስትር ውስጥ ካሉ ግዥዎች ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ሙስናዎችን እንዲመነጥር ለኤፍኤስቢ የነገሩት። ከምክትል ሚኒስትሩ ጋር ሌሎች የታሰሩት ሰዎች መኖራቸውን ዘገባው ጠቅሷል።

# በራሱ የሚተማመንና ሙስናን የሚፀየፍ ትውልድ መገንባት የሁሉም ኃላፊነት መሆኑ ተገለፀ





የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 በሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ክበብ አደረጃጀት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱ ተገልጿል።

በት/ቤቶች የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ክበብ በማቋቋምና በማጠናከር ብሩህ ተስፋ ያለውና ተስፋ የተጣለባቸው ትውልድ መገንባት የሁሉም ኃላፊነት መሆኑን የወረዳው የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍል ቡድን መሪ አቶ በላይነህ ዘርፉ ገልፀዋል።

በ1ኛ ደረጃ ት/ቤት የክበብ አደረጃጀትን ለማጠናከር ለክበባት ስራ አስፈፃሚ አባላት ግንዛቤ መፈጠሩን ቡድን መሪው መጥቀሳቸውን ከአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የፌስቡክ ገፅ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

አቶ በላይነህ አክለውም ስልጠናው የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና አባላት የክበቡን ተግባርና አላማ በመረዳት በዋናነት በራሱ የሚተማመን እውቀትና ብቃት ያለው፣ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚወደድና የሚመሰገን እንዲሁም ሙስናን የሚፀየፉ ትውልድ መገንባት እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል።

# ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ከመንግስት ባለፈ የሁሉም ዜጎችና ተቋማት ርብርብ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት



ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ከመንግስት ባለፈ የሁሉም ዜጎችና ተቋማት ርብርብ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ገለጸ። ኢትዮጵያ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የፀረ-ሙስና ስምምነቶችን በመቀበል እና ሀገራዊ የህግ ማዕቀፎችን በማውጣት ለተግባራዊነቱ ጥረት እያደረገች ትገኛለች። በተለይም ከለውጡ በኋላ የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል።

በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደ ሀገር ስር የሰደደውን ሌብነት ለመከላከል ሰባት አባላት ያሉት ብሔራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ እንዲቋቋም ማድረጋቸው ይታወቃል።የተቋቋመው ብሔራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን በመቀበል እንደ ሀገር ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል

የህዝብና መንግስት ሀብት ከምዝበራ ማዳን እንደተቻለ በሪፖርቱ አረጋግጧል።

በፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ገዛኸኝ ጋሻው ለኢዜአ እንዳሉት፤ ኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ፣ የሙስና መከላከል ስራዎችን እያከናወነ ነው።

ከፌዴራል፣ ከክልሎችና ከሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ጋር በመቀናጀት ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና እየሰጠ መሆኑን ገልጸዋል።

የኃይማኖት ተቋማት፣ ሲቪክ ማህበራትና የትምህርት ተቋማትን አስተባብሮ የሥነምግባር ትምህርት በመስጠት የህብረተሰቡን ሙስና እና ብልሹ አሰራር የማጋለጥ ባህል ማሳደግ ተችሏል ብለዋል።

ኮሚሽኑ ጥናት በማካሄድና የሃብት ምዝገባ በማከናወን ሙስናን ቀድሞ ከመከላከል ባለፈ፤ በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት በዲጂታል እና በተለያዩ አማራጮች ከቀረቡ 85 ጥቆማዎች

ውስጥ 65 የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን ለፍትህ አካላት ቀርቦ ምርመራ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

በዚህም እንደ ሀገር በተሰራ 373 የአስቼኳይ ሙስና መከላል ሥራዎች በማከናወን ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ የህዝብና መንግስት ሃብት እንዲሁም ከ23 ሚሊዮን ካሬ ሜትር በላይ የከተማ እና ገጠር መሬት ከምዝበራ ማዳን መቻሉን አስታውሰዋል። በ25 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት የሙስና ስጋት ያለባቸው ዘርፎችን አሰራር በማጥናት በውጤቱ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ እየተደረገ መሆኑን መግለፃቸውን ኢዜአ ዘግቧል። ኮሚሽኑ በሀብት ምዝገባ፣ በእድሳትና አገልግሎት በማቋረጥ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን እየሰራ መሆኑንም አስታውቀዋል። መንግስት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በትኩረት እየሰራ መሆኑን ገልጸው፥ ጉዳዩ የሁሉንም ግለሰቦችና ተቋማት ርብርብ የሚፈልግ መሆኑን ገልፀዋል።

## ከ40 ሚሊየን ብር በላይ የአልባሳት ግዢ ጋር ተያይዞ በሙስና ወንጀል የተከሰሱት ጥፋተኛ ተባሉ

ከ40 ሚሊየን ብር በላይ የአልባሳት ግገር ጋር ተያይዞ በከባድ የሙስና ወንጀል የተከሰሱት የጥፋተኝነት ፍርድ ተላልፎባቸዋል። የጥፋተኝነት ፍርድ የተላለፈባቸው የቀድሞ የአዲስ አበባ እሳት እና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር ሰለሞን ፍስሃ እና ነጋዴ የሆኑት ንጉስ አማን ናቸው። ሌሎች የኮሚሽኑ ሰራተኛ የነበሩ 5 ግለሰቦች ደግሞ በተከሰሱበት ድንጋጌ እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቷል። በዚሁ መዝገብ 3ኛ ተከሳሽ የነበረው የኮሚሽኑ የለውጥ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ባለሙያ ደረጄ ተፈራ ነጻ ተብሏል። ብይኑን የሰጠው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው።

የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በ2015 ዓ.ም መጨረሻ በ8 ተከሳሾች ላይ ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ መመስረቱ ይታወሳል። ክሱ ተመስርቶባቸው የነበሩ 1ኛ ኮሚሽነር ሰለሞን ፍስሃ፣ 2ኛ የተቋሙ የመንግስት ግዢ ዳይሬክተር ግሩም ወልዴ፣ 3ኛ ደረጄ ተፈራ፣ 4ኛ የኮሚሽኑ የሎጂስቲክስ ምዝገባና ቁጥጥር ባለሙያ ወንድሜነህ ምስጋናው፣ 5ኛ የአደጋ ስጋት ትግበራ ቡድን መሪ እዮብ ታደሰ ካሳ፣ 6ኛ በኮሚሽኑ የህክምና ባለሙያዋ ሲስተር አልማዝ ጌቶ፣ 7ኛ የአደጋ መረጃ ሀርድ ዌርና ሶፍትዌር ባለሙያ መስፍን ለገሰና 8ኛ ንጉስ አማን ናቸው።

ከተከሳሾች መካከል 1ኛ እና 8ኛ ተከሳሾች ፍርድ ቤት ያልቀረቡ ሲሆን÷ ቀሪ ተከሳሾች ግን ቀርበዋል። ዐቃቤ ሕግ በተከሳሾቹ ላይ የተሳትፎ ደረጃ ጠቅሶ ባቀረበው የከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ላይ እንደተመላከተው በሰኔ ወር በ2014 ዓ.ም ከ1ኛ እስከ 7ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች የግዢ ጨረታ ሂደት ውስጥ በመሳተፍና በመመሳጠር፣ በወቅቱ በተደረገ የገበያ ዳሰሳ ጥናት ቡልዶዘር የተሰኘ የእሳት አደጋ መከላከያ የአልባሳት ዋጋ በፍሬ 46 ሺህ 923 ብር እያለ ተከሳሹቹ ግን በከፍተኛ ዋጋ ማለትም አንዱን 184 ሺህ 644 ብር በሆነ የገንዘብ መጠን ከ8ኛ ተከሳሽ ተጫራች ድርጅት ግገር እንዲፈጸም አፅድቀዋል በማለት በክሱ አስፍሮ ነበር።

አጠቃላይ 217 ፍሬ አልባሳትን በ40 ሚሊየን 67 ሺህ 748 ብር ግገር እንዲፈጸም በማድረግ በመንግስት ላይ በልዩነት 29 ሚሊየን 885 ሺህ 441 ብር ጉዳት እንዲደርስ አድርገዋል ብሎ በክስ ዝርዝሩ ላይ ዐቃቤ ሕግ ጠቅሶ ነበር። ከ1ኛ እና ከ8ኛ ተከሳሾቹ ውጪ ያሉ ቀሪ ተከሳሾች የክስ ዝርዝሩ ከደረሳቸው በኋላ ክሱ እንዲሻሻልላቸው የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ በጽሁፍ ማቅረባቸውን ተከትሎ የግራ ቀኝ ክርክርን ፍርድ ቤቱም መርምሮ ክሱ እንዲሻሻል የቀረበው ጥያቄ የሕግ አግባብነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎት ነበር። ተከሳሾቹ የቀረበባቸው ክስ ላይ የተመላከተውን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸማቸውን ጠቅሰው÷ የዕምነት ክህደት ቃላቸውን በመስጠታቸው ዐቃቤ ሕግ የሰው ምስክርና የሰነድ ማስረጃ አቅርቧል።

ፍርድ ቤቱም በዐቃቤ ሕግ የተሰሙ ምስክሮችን ቃልና ማስረጃ መርምሮ በዛሬው ቀጠሮ 2ኛ ተከሳሽ ግሩም ወልዴ፣ 4ኛ ተከሳሽ ወንድሜነህ ምስጋናው፣ 5ኛ እዮብ ታደሰ ካሳ፣ 6ኛ ሲስተር አልማዝ ጌቶ እና 7ኛ ተከሳሽ መስፍን ለገሰን በሚመለከት በዓቃቤ ሕግ በቀረበ ማስረጃ የወንጀል ድርጊቱ መረጋገጡን ገልጾ በተከሰሱበት ድንጋጌ እንዲከላከሉ ብይን መሰጠቱን ኤፍቢሲ ዘግቧል። በዚሁ መዝገብ በ3ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰውን ደረጄ ተፈራ በሚመለከት በዐቃቤ ሕግ በቂ ማስረጃ አልተሰማበትም በማለት ፍርድ ቤቱ ነጻ ብሎታል።

በነዚህ ጥፋተኛ በተባሉ በሁለቱ ተከሳሾች ላይ ዐቃቤ ሕግ በቀጣይ ቀጠሮ የቅጣት ማክበጃ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ተብሏል። ፍርድ ቤቱ ተከላከሉ የተባሉ አምስቱ ተከሳሾችን የመከላከያ ማስረጃ ካላቸው ለመጠባበቅ ለግንቦት 19 ቀን 2016 ዓ.ም ተቀጥሯል።

## በሥነምግባር አርአያ የሆነና ሌብነትን የሚጠየፍ ትውልድ ለማፍራት የሥነምግባር ክበባትን ማጠናከር ያስፈልጋል



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክ/ከተማ ለሚገኘው ለጠመንጃ ያዥ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 30 ኮምፒውተሮች ድጋፍ አድርጓል።

በድጋፍ ሥነስርዓቱ የተገኙት የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ እንደተናገሩት ኮሚሽኑ ከሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት አንዱ የትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ሲሆን፣ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በሥነምግባር የታነፁ የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ የሚፈጠሩባቸው እንደመሆናቸው መጠን ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

አቶ ተስፋዬ አክለውም የጠመንጃ ያዥ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሥነምግባራቸው ለሌሎች ትምህርት ቤቶች ሞዴል እንዲሆኑ የሥነምግባር ክበባት በማቋቋም በሥነምግባር የታነፀ ትውልድ ለማፍራትና ተግተው እንዲሠራ ኮሚሽኑ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ጋር በትስስር ክትትል እንደሚያደረግ አስታውቀዋል።

የትምህርት ቤቱ የሥነምግባር



ክበባት በደንብ ተደራጅተው የተለያዩ የሥነምግባር ትምህርቶችንና ስልጠናዎችን በመስጠት ሌሎች ትምህርት ቤቶችም ተሞክሮና አርዓያነት የሚወስድበት እንዲሆን መሥራት እንደሚያስፈልግ በአፅንዖት ገልፃዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የአውታሮች መከታተያ ዳ/ዳይሬክተር አቶ አምባላይ ዘርአይ በበኩላቸው በኮሚሽኑ ለተደረገው ድጋፍ አመስግነው፣ ክበባትን ለማጠናከር በትኩረት እንደሚሰራ ገልፀዋል።

በሥነምግባሩ የታነፀ ትውልድን ለማፍራትና የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የኮምፒውተር እጥረት ዋነኛ ችግር ነው ያሉት የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አቶ ደሳለኝ ታዬ፤ አንድ ኮምፒውተር ለ5 ተማሪዎች



የሚሰጥበት ሁኔታ ለመቅረፍ ኮሚሽኑ ባደረገው ድጋፍ ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማቸው ተናግረዋል።

አቶ ደሳለኝ አክለውም የኮፒውተር ድጋፉ የመማር ማስተማር ሂደቱን የሚያሳልጥ ከመሆኑም ባሻገር የተለያዩ የሥነምግባር ትምህርቶችን በሚኒ ሚዲያ እና በራሪ ወረቀቶችን በመጠቀም ለመስራት እንደሚያስችልና በቀጣይም ስራውን አጠናክረን እንቀጥላለን ብለዋል፡

የሥነምግባር ክበብ አባላት በበኩላቸው በሥነምግባር የታነፀ ትውልድ ለማፍራት የተለያዩ የግንዛቤ ስራዎች እየተሰሩ በመሆኑ የሚደረጉ ድጋፎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል።

በጠመንጃ ያዥ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 961 ተማሪዎች እና 93 መምህራን እንደሚገኙ ተገልጿል።

# የኮሚሽኑ አመራሮች ከህዝባዊ ድርጅቶች ኃላፊዎች ጋር በጋራ በሚሰሩባቸው ጉዳዮች ላይ ውይይት አካሄዱ





የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች ከህዝባዊ ድርጅቶች ኃላፊዎች ጋር በጋራ በሚሰሩባቸው ጉዳዮች ላይ ውይይት አካሄደዋል፡፡

በመድረኩ ኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ሥራ ከህዝባዊ አደረጃጀቶች ጋር የሚሰራበት የህግ ማዕቀፍ፣ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ሚና እንዲሁም ሙስናን መከላከል ካልተቻለ በሀገር ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ የሚያሳይ ሰነድ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ እንዲሁም ህዝባዊ ተቋማት የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ተግባራትን ለማከናወን በየተቋማቸው የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት በሚፈጠርበት ሂደት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

## ኮሚሽኑ አዲስ ለተመደቡ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያዎች ሥልጠና ሰጠ





የሲዳማ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አዲስ ለተመደቡ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለአምስት ተከታታይ ቀናት በአለታ ጩኮ ከተማ ስልጠና ሰጠ፡፡

በስልጠናዉ ማጠቃለያ መድረክ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የክልሉ ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ወ/ሮ ዘላለም ለማ እንደገለፁት ስልጠናዉ አዲስ ለተመደቡ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያዎች በቀጣይ የሚሰሩትን ተግባር በሚገባ ተረድተዉና በቂ እዉቀት ጨብጠዉ እንዲሰሩ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ኮሚሽነሯ አክለውም የሙስና ወንጀል ረቂቅነትና በህዝባችን ላይ የሚያደርሰዉን አሉታዊ ተጽእኖ በብቃት ለመታገል ዝግጁ የሚያደርጋቸዉ እንደሆነ መገለፁን የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡

## የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ከደቡብ ኮሪያ የፀረ-ሙስና እና ሲቪል መብቶች ኮሚሽን (ACRC) ከፍተኛ አመራሮች ጋር ውይይት አካሄዱ




ምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያዎች በቀጣይ የሚሰሩትን ተግባር በሚገባ ተረ የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥራ ኃላፊዎች ከደቡብ ኮሪያ የፀረ-ሙስና እና ሲቪል መብቶች ኮሚሽን (ACRC) ከፍተኛ አመራሮች ጋር ውይይት አካሄደዋል፡፡

ውይይቱ በሁለት ዓበይት ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ በአቅም ግንባታ ስልጠና እና በአለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ስምምነት (UNACC) ትግበራ አፈጻጸም ላይ ያተኮረ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በውይይቱም የደቡብ ኮሪያ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ዙሪያ ለፌዴራል፣ ለክልል እና ከተማ አስተዳደር የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች እንዲሁም በየተቋማቱ ተመድበው ለሚሰሩ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊዎች ስልጠና ለመስጠት እና በአለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ስምምነት (UNACC) አፈጻጸምና አተገባበር ላይ ልምድ ለመለዋወጥ የጋራ መግባባት ላይ መደረሱ ተጠቁሟል፡፡

# ሀገር አቀፍ የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የ2016 በጀት አመት የ9 ወራት የሥራ አፈፃፀም ግምገማ አካሄዱ





የፌደራል፣ የክልል እና የከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነሮች እና ም/ኮሚሽነሮች እንዲሁም የኮሚሽነሩ መሪ ሥራ አስፈፃሚዎች በተገኙበት ሀገር አቀፍ የ2016 በጀት አመት የ9 ወራት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ቀርቦ ግምገማ ተካሄዷል፡፡

ሀገር አቀፍ የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የትስስር ጉባኤ አባላት በተገኘበት የፌደራል፣ የክልል እና የከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች ሪፖርታቸውን ያቀረቡ ሲሆን፥ በሪፖርታቸውም በዘጠኝ ወራት ውስጥ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ቀርቧል፡፡

በአሰቸኳይ ሙስና መከላከል፣ በሥነምግባር ግንባታ፣ በጥቅም ግጭት መለየትና ማጣራት፣ በሙስና መረጃ አያያዝ እና የሙስና መከላከል ሥራን ውጤታማ የማድረግና በዘርፍ ተቋማት እስከ ወረዳ ድረስ ላይ የሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን የመደገፍና አቅም ግንባታ የመስጠት እንዲሁም የፀረ-ሙስና ትግሉን የተሳለጠ በማድረግ በርካታ ስራዎች መሰራታቸው ከቀረበው ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

እንዲሁም አቅምን ከመገንባት አኳያ የተለያዩ ስልጠናዎች እና ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ የተሰራ ሲሆን፣ በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች የታዩ ክፍተቶችን እስከ ተቋማት ድረስ በመሄድ ለመፍታት መሞከሩ ተገልጿል፡፡

በቀረበው የ9 ወራት አፈፃፀም በርካታ ተግባራት መሰራታቸውንና ክፍተቶችን በማረም ለቀጣይ ሶስት ወራት ቀሪ ተግባራትን ትኩረት በመስጠት መሰራት እንዳለበት ተመላክቷል፡፡ ለቀጣይ ስራ በቁርጠኝነት እና በተነሳሽነት መንፈስ በጋራ መስራት እንደሚገባ ተገልጿል፡፡

# የሥነ-ምግባር ጥሰት በፈፀሙ 52 አመራሮችና ሠራተኞች ላይ እርምጃ ተወሰደ

ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከቀረቡ 95 ጥቆማዎች 36 አመራሮችና ሠራተኞች ጥፋተኛ መሆናቸው በመረጋገጡ እርምጃ መወሰዱን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የቀሪዎቹ ጉዳይ ደግሞ በዲሲፕሊን ኮሚቴ በመታየት ሂደት ላይ እንደሚገኝ ተመላክቷል፡፡ በተጨማሪም በ2015 በጀት ዓመት ጥቆማ ቀርቦባቸው እርምጃ ሳይወሰድባቸው በሂደት ላይ በሚገኙ ጉዳዮች ላይ ክትትል ተደርጎ በ16 አመራሮችና ሠራተኞች ላይም አሥተዳደራዊ እርምጃ ተወስዷል ብሏል ተቋሙ፡፡

ባጠቃላይ ካለፈው በጀት ዓመት ተላልፈው በሂደት ላይ የነበሩ ጥቆማዎችን ጨምሮ በ52 የተለያዩ የሥነ-ምግባር ጥሰቶች 108 አመራሮችና ሠራተኞች ጥቆማ ቀርቦባቸዋል መባሉን ከአገልግሎቱ ያገኘነው መረጃ አመላክቷል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
Ethiopian Electric Utility

ከነዚህ መካከልም 17 የጽሁፍ፣ 31 የደመወዝ፣ 2 ስንብት፣ አንድ ሠራተኛ ከደረጃ የማንሳት እና አንድ ሠራተኛ ነጻ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ የቀሪ 54 ሠራተኞችና ኃላፊዎች ጉዳይ ደግሞ በሂደት ላይ እንደሚገኝ ነው የተመላከተው፡፡

## የመሬት ግብይት ስርዓትን በማዘመን ብልሹ አሰራሮችንና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት እንደሚገባ ተገለጸ

የሰሜን ሸዋ ዞን ምክትል አስተዳዳሪ አቶ ተክለየስ በለጠ መድረኩን ሲከፍቱ እንደገለጹት መሬት የሁሉም ሀብት መሠረት መሆኑን ጠቅሰው፣ በዚያው ልክ ለብልሹ አሰራርና ለመልካም አስተዳደር ጉድለት የተጋለጠ መሆኑን አስረድተዋል፡

የመሬት ግብይት ስርዓትን በማዘመን ብልሹ አሰራሮችንና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት እንደሚገባ አስታውቀዋል፡፡ በዞኑ ባለፉት ዓመታት በርካታ ስራዎች መከናወናቸውን ጠቅሰው፣ አሁንም በ22 ወራዳዎችና በ381 ቀበሌዎች እየተተገበረ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

ስራውን በአግባቡ መተግበር ትርጉሙ ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ ተክለየስ፣ በቀጣይም የመሬትን ግብይት ዘመናዊና ቀልጣፋ በማድረግ ህገወጥነትን በመከላከል ህዝብና መንግስትን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

የሰሜን ሸዋ መሬት መምሪያ ተወካይ አቶ ክብረቴ ቅጣው እንደገለጹት መሬት ትልቁ ሀብት መሆኑን ጠቅሰው ሀብቱን በሲስተም በዘመናዊ የአሰራር ስርዓት ለማስተዳደር እየተሰራ መሆኑን አንስተዋል፡፡ በዚህም ዞኑ የተሻለ አፈፃጸም ማስመዝገቡን ጠቁመዋል፡፡

## የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና አባላት በኮሚሽኑ የመስክ ጉብኝት አካሄደ





የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና አባላት በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በመገኘት የመስክ ጉብኝት አካሄደዋል፡ ፡የመስክ ጉብኚቱ የኮሚሽኑ የስራ ከባቢ ይበልጥ ምቹ ከሆነ ወዲህ እንዲሁም ቋሚ ኮሚቴው በአዲስ መልክ ከተዋቀረ በኋላ የተደረገ የመጀመሪያው ጉብኝት ነው።በጉብኝቱ ወቅት የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ስለ ኮሚሽኑ አደረጃጀት፣ የሥራ አካባቢ እና የሚያከናውኗቸው ተግባራትን የሚመለከት ገለጻ አድርገዋል።

በገለፃውም የኮሚሽኑ አደረጃጀት፣ ተጠሪነት፣ ጥቅማጥቅም እና ተያያዥ ተግዳሮቶች የተፈለገውን የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ተግባር ከግብ ለማድረስ እንቅፋት እንደሆነባቸው ተናግረዋል።

የቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው የፀረ-ሙስና ትግሉን ዳር ለማድረስ በቀጣይ ኮሚሽኑን የመደገፍ እና የመከታተል ስራን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልፀው፥ ሙስና በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተባባሰ በመምጣቱ ሁሉም አካላት የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንደሚኖርበት አስገንዝበዋል፡ ፡ ኮሚሽኑ ብዙ ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ አበረታች ስራዎችን እየሰራ መሆኑን ገልፀው፥ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚከናወኑ ተግባራት በቀጣይ ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ጠቁመዋል።



በተለይ ሚዲያ ለፀረ-ሙስና ትግሉ አጋዥ መሆን አለበት ብለዋል። ክቡር እሸቴ አስፋው የሙስና መከላከል ዘርፍ ም/ኮሚሽነር፥ በድጋፍና ክትትል የተሰጠንን ምክረ ሀሳብ በማገም በቀጣይ የተሻለ ስራ እንሰራለን ብለዋል፡

የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ስራዎችን ከክልል እና ከከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ጋር በመቀናጀት እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል። ክቡር ወዶ አጦ የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ም/ ኮሚሽነር በበኩላቸው የቋሚ ኮሚቴ አባላት የሚያደርጉት የድጋፍና ክትትል ሥራ ለኮሚሽኑ ትግል አቅም እንደሚሆን ገልፀዋል።

## ዩናይትድ ስቴትስ አራት የቀድሞ የማላዊ መንግሥት ባለሥልጣናት በከፍተኛ ሙስና ውስጥ በመሳተፋቸው ሀገሯ እንዳይገቡ መከልከሏን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የተከለከሉት ባለሥልጣናት የማላዊ የቀድሞ የህግ አማካሪ እና የፍትህ ፀሀፊ ሬይኔክ ማትምባ፣ የመንግሥት ግዥዎችና የንብረት ማስወገድ ዳይሬክተር የነበሩት ጆን ሱዚ ባንዳ፣ የቀድሞ የፖሊስ አገልግሎት ጠበቃ ሙዋቢ ካሉባ እና የፖሊስ አገልግሎት የቀድሞ ዋና ኢንስፔክተር ጆርጅ ካይንጃ መሆናቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስታውቋል። አራቱ ባለሥልጣናት መንግሥታዊውን የፖሊስ ተቋም የሥራ ውል አሳልፎ



ለመበጠተ ከሣል የንግድ ድርድተ ባለቤት "ጉቦ እና ሌሎች ዋጋ የሚያወጡ መደለያዎችን በመቀበል የተሰጣቸውን የህዝብ ሥልጣን አለአግባብ ተጠቅመዋል" ሲል የሚኒስቴሩ መግለጫ አመልክቷል።

"ዩናይትድ ስቴትስ ለሙስና የተጋለጡ ባለሥልጣናትን በተጠያቂነት በመያዝ በመንግሥት የግዥ ሂደቶች ግልጽነት እና ታማኝነትን በማበረታታት በሀገራቸው ፍትህ እና ብልጽግና ለማስፈን ከሚሰሩት የማላዊ ዜጎች ጋር ትቆማለች።" ሲሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ማቲው ሚለር አስታውቀዋል። የማላዊው ፕሬዝዳንት ላዛረስ ቻኩዌራ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሙስና ላይ ዘመቻ ከፍተዋል። እ.አ.አ በጥር ወር 2022 ዓ.ም የሙስና ወንጀል ክስ በተመሰረተባቸው ሶስት ሚኒስትሮች ሳቢያ ካቢኔውን በሙሉ መበተኑ ተመላክቷል።

በዚያው ዓመት መገባደጃ ላይ የማላዊ ፀረ-ሙስና ቢሮ ምክትል ፕሬዝዳንቱን ሳሎስ ክላውስ ቺሊማን በሌብነት ከሶ አስሯል። የፀረ-ሙስና ቡድኑ በሀገሪቱ የመንግሥት የግዥ ስርዓት ኮንትራት አሰጣጥ ላይ ተጽእኖ በማድረግ የመንግስት ሃብት ዘርፈዋል ያላቸውን የማላዊ መንግስት ባለስልጣናት ሲመረምር መቆየቱን ተዘግቧል።

# የትራንስፖርት ስምሪትና የነዳጅ ድጎማን በማጭበርበር የሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ የስምሪት ኃላፊዎችና የትራንስፖርት ማህበራት አመራሮች ዋስትና እንዲታገድ ተጠየቀ



የትራንስፖርት ስምሪት እና የነዳጅ ድጎማን በማጭበርበር የሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ የስምሪት ኃላፊዎችና የትራንስፖርት ማህበራት አመራሮች ዋስትና እንዲታገድ ተጠየቀ፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ጊዜ ቀጠሮ ችሎት በቀጠሮው በአዲስ አበባ መናኸሪያዎች የሚገኙ የመንገድ ትራንስፖርት ቅርጫፍ የስምሪት ኃላፊዎች፣ የትራንስፖርት ማህበራት አመራሮችና በነዳጅ ድጎማ ውስጥ ተሳታፊ ናቸው ተብለው የተጠረጠሩ ደላሎችን ጉዳይ ተመልክቷል፡፡

ከብሔራዊ መረጃ ደህንነት ተቋም ጋር በጋራ በመሆን ተጠርጣሪዎቹን በቁጥጥር ስር አውሎ የምርመራ ስራ እያከናወነ የሚገኘው የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን መርማሪ የሰራውን የምርመራ ማጣሪያ ስራ እና ቀሪ ምርመራዎችን በዝርዝር አቅርቦ ከጠበቆች ጋር ክርክር ተደርጓል፡፡ተጠርጣሪዎቹ የቀድሞ የህዝብ ትራንስፖርት የተሽከርካሪ ዘርፍ ኃላፊ እና የትራንስፖርት ሎጂስቲክ ሚኒስቴር አማካሪ የነበሩት ከድል ማግስት ኢብራሂም በከር፣ የትራንስፖርት ማህበራት አመራርና አባል ታምራት በየነ፣ ጌትነት በየነ እንዲሁም የመናኸሪያ የትራንስፖርት ስምሪት ኃላፊዎች አበበ ወ/መስቀል፣ ሺመት መሸሻ፣ ታምራት ለገሰ፣ ጥበቡ ተፈሪ፣ እንግዳ ሽኩር፣ ባርናባስ አለሙ፣ ሙስጠፋ ጀማል እና ይታገሱ ተድላ ይገኙበታል፡፡

መንግስት ህዝብን በትራንስፖርት አገልግሎት ለመደገፍ ለህዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ማህበራትን የነዳጅ ድጎማ እንዲያገኙና አገልግሎቱን እንዲሰጡ ለማስቻል ባዘጋጀው የድጎማ መርሐ ግብር ላይ በጥቅም በመመሳጠር የነዳጅ ድጎማን በማጭበርበርና ለግል ጥቅም በማዋል መንግስት ላይ ከ34 ሚሊየን ብር በላይ ክፍያ እንዲፈጽምና ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ የሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ መሆናቸውን ጠቅሶ፥ ፖሊስ የተጨማሪ ምርመራ ጊዜ ቀጠሮ መጠየቂያ አቅርቧል፡፡

በተጨማሪም ፖሊስ ከአንድ በላይ ተሽከርካሪ ያላቸው ባለንብረቶች በሙሉ የመስመር ስምሪትን ለራሳቸው በመያዝ፣ ለሁሉም ማህበሮች ኮንትራት እንዲሰጥ ጨረታ ሲወጣ ጨረታውን በማጭበርበር ለራሳቸው በመውሰድ፣ ለስምሪትና ለመንገድ ትራንስፖርት ኃላፊዎች ጉቦ በመስጠት፣ የስምሪት ቦታ ሳይወጡ ለህዝብ አገልግሎት ሳይሰጡ የነዳጅ ድጎማውን ወስደው የራሳቸውን የኮንትራት ስራ መስራት፣ ምንም አይነት አገልግሎት ሳይሰጡ የክፍያ ተጠቃሚ መሆን፣ በተበላሹና በቆሙ ተሽከርካሪዎችና በሀሰተኛ ታርጋ ቁጥሮች የነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚ መሆንና፣ ከነዳጅ ማድያዎች ጋር በመመሳጠር በሊትር ኮሚሽን በመያዝ በድጎማ የሚቀዱትን ነዳጅ በጥቁር ገበያ መሸጥና በመንግስት ላይ ጉዳት ማድረስ የሚሉ ነጥቦችን ጠቅሶ ለጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ በዝርዝር አቅርቧል፡፡

በዚህ መልኩ መርማሪ ፖሊስ ከዚህ በፊት በተሰጠው የምርመራ ማጣሪያ ጊዜ ውስጥ የ11 የተጠርጣሪዎችን ቃልና እና የ9 ሰዎች ምስክሮችን ቃል መቀበሉን፣ የቴክኒክ ማስረጃዎች እንዲሰጡት የሚመለከተውን ተቋም መጠየቁን ገልጿል፡፡

ቀረኝ ያላቸውን ማለትም ቀሪ ምስክሮችን የመቀበልና ከተቋማት ማስረጃዎችና የኦዲት ሪፖርት የማቅረብ ስራ እንደሚቀረው ጠቅሶ፥ በወ/መ/ስ/ህ/ ቁጥር 59/2 መሰረት የ14 ቀን ጊዜ ቀጠሮ እንዲሰጠው ጠይቋል፡፡

ተጠርጣሪዎቹ ጠበቆች በኩል በፖሊስ የተጠቀሰውን የጊዜ መጠየቂያ ምክንያቶች ተጨማሪ ጊዜ ለማስጠት አሳማኝ አይደሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በፊት በነበረ ቀጠሮ ኦዲት ሪፖርት ለማቅረብ እና የ30 ሰው ምስክር ቃል ለመቀበል በሚል በተመሳሳይ ጊዜ ቀጠሮ መጠየቁን አስታውሰው፥ በድጋሚ መጠየቁ ተገቢ አይደለም በማለት የመከራከሪያ ነጥብ አንስተዋል፡፡

ማን ምን አደረገ የሚለው የተጠርጣሪዎች ተሳትፎ በኦዲት ሪፖርት ተለይቶ ባልቀረበበት ሁኔታ ላይ ግለሰቦቹ በስር ሆኖ ሊቆዩ አይገባም በማለት የደንበኞቻቸው የዋስትና መብታቸው እንዲከበርላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፖሊስ በበኩሉ በጠበቆች ለተነሱ የመከራከሪያ ነጥቦች ላይ መልስ የሰጠ ሲሆን፣ በዚህም ተጠርጣሪዎቹ በስር ላይ ሆነው ምስክሮች ላይ በመናኸሪያ ውስጥ በሚሰሩ ግለሰቦች በኩል ማስፈራሪያ እየደረሰባቸው መሆኑን አመልክቷል፡፡ ተጠርጣሪዎቹ ቢወጡ ምስክር ሊያስፈራሩ እና ካላቸው ደረጃ አንጻር ማስረጃ ሊያጠፉበት እንደሚችሉ ስጋቱን በመጥቀስ ዋስትና ጥያቄያቸውን በመቃወም መልስ ሰጥቷል፡፡

መዝገቡን በተመለከቱት የችሎቱ ዳኛ በኩል ምስክርን በሚመለከት ተጨማሪ ጊዜ ያስፈለገበት ምክንያትን ፖሊስ እንዲያብራራ በቀረበ ጥያቄ መሰረት ፖሊስ ቀሪ ምስክሮች ከአዲስ አበባ ውጪም የሚገኙ መኖራቸውን ጠቅሶ፥ በብሔራዊ መረጃ ደህንነት በኩል የሚመጡ ምስክሮች ቃል እንደሚቀበልና ቀሪ ምስክሮችን ለመቀበል ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልገውና ምስክሮች በፍጥነት እንዲመጡ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጾ መልስ ሰጥቷል፡፡

“የሚሰበሰቡ ማስረጃዎችን በሚመለከት ግለሰቦቹ ማስረጃ የማጥፋት አቅም አላቸው ወይ? “ተብሎ በዳኛ በኩል ለቀረበው ጥያቄ መልስ የሰጠው ፖሊስ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎች እንደመሆናቸው ከመስሪያ ቤታቸው የሚመጡ ማስረጃዎችን ሊያጠፉ ይችላሉ በማለት ስጋቱን ገልጿል፡፡

ተሳትፏቸው አልተጠቀሰም ለሚለው የጠበቃ መቃወሚያን በሚመለከት ከመንገድ ትራንስፖርት የሚመጣ ወርኃዊ ስምሪት መሰረት መስመርተኛ እያለ የሚፈልጉትን የመስመር ስምሪት ለሚፈልጉት ሰው በመስጠትና በጥቅም በመመሳጠር እረገድ ማን ምን ተሳትፎ አለው የሚለውን ለማሳያ የእያንዳንዱን ተሳትፎ ማቅረቡን ጠቅሶ፥ ተሳትፏቸውን በኦዲት ሪፖርት ለማረጋገጥ ማረጋገጫ እንዲመጣ መጠየቁን አንስቷል፡፡

የግራ ቀኝ ክርክሩን የተመለከተው ጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ ፖሊስ ቀረኝ ካላቸው ስራዎች አንጻር ተጠርጣሪዎቹ ቢወጡ ማስረጃ ሊያጠፉ የሚችሉበት እድል ሊኖር አይችልም የሚለውን ግምት በመያዝ ተጨማሪ ጊዜ ቀጠሮ መፍቀድ ተገቢነት የለውም በማለት ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪዎቹ የ50 ሺህ ብር ዋስ አሲዘው ከስር እንዲፈቱ የፈቀደ ቢሆንም ፖሊስ በመዝገቡ ላይ ይግባኝ ብሏል፡፡

በአዲስ አበባ መናኸሪያዎች የሚገኙ የመንገድ ትራንስፖርት ቅርጫፍ የስምሪት ኃላፊዎች፣ የትራንስፖርት ማህበራት አመራሮችና በነዳጅ ድጎማ ውስጥ ተሳታፊ ናቸው ተብለው የተጠረጠሩ ደላሎችን ጉዳይ

# በባንክ ብድር አቅርቦት ላይ የተጋረጠው ሙስና ለንግድ ማኅበረሰቡ ፈተና መሆኑ ተገለጸ

የአገሪቱ ሁሉም ባንኮች ብድር ለማቅረብ የሚያስችሉ መሥፈርቶች ቢኖሯቸውም፣ ብድር የሚፈቅዱ አካላት የሚፈጽሙት ሙስና የንግድ ማኅበረሰብን ፈተና ውስጥ መክተቱ ተገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ‹‹የብድር አቅርቦት በቢዝነስ ላይ ያለው ተፅዕኖ›› በሚል ርዕስ ባዘጋጀው የውይይት መድረክ የተገኙ የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት፣ ብድር ለማግኘት የሚጠየቁት ጉቦ እንዳስመረራቸው ተናግረዋል፡፡

የብድር አቅርቦቱን በሚፈለገው መጠን ተደራሽ ለማድረግ ሁሉም ባንኮች በሚባል ደረጃ የገንዘብ እጥረት እንዳለባቸው በውይይቱ ላይ የተነሳ ሲሆን፣ ያለውን የብድር አቅርቦትም ቢሆን መሥፈርቱን ላሟላ ትክክለኛ ተበዳሪ ተደራሽ ከማድረግ ይልቅ በሙስና መፈቀዱ ችግሩን የከፋ አድርጎታል ብለዋል፡፡

ጉርሻ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ አክሲዮን ማኅበርን በመወከል በውይይት መድረኩ የተገኙት አቶ ሁንልኝ ጥጋቡ




በአሁኑ ጊዜ የባንክ ብድር በሙስና እንደሚሰጥ ሁሉም የሚያውቀው ነው ብለው፣ ‹‹ብድር የሚፈቀደው በሙስና ነው፣ ሙስናው ደግሞ ከፖለቲካ ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ከዚህ በላይ ችግሩን ዘርዝሮ መግለጽ ይቻላል፤›› ሲሉ አስረድተዋል፡፡ ችግሩን መቅረፍ ካስፈለገ ስለጉዳዩ በግልጽ መነጋገር እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል፡፡

አቶ ሁንልኝ እንደሚሉት፣ ባንኮች ውስጥ በሚፈጸሙ ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶች ምክንያት ብድር ማግኘት አልተቻለም፡፡‹‹ችግሩን ሁሉም ሰው የሚያውቀውና በየኮሪደሩ የሚሰማ ነው፤›› ያሉት የአፍሪካ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ፕሮግራም ኃላፊ አቶ ጌታቸው ተክለ ማርያም ናቸው፡፡ የባንክ ብድርን ጥቂት ግለሰቦች መቆጣጠራቸውን፣ ባንኮች ውስጥ ብድር እንዲፈቀድ የሚወስኑ ግለሰቦች የአዋጭነት ጥናት በእጅ አዙር እንደሚሠሩና በብድር አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ያሉ ሁሉም ሰዎች ምርመራ ሊደረግባቸው ይገባል ብለዋል፡፡ ‹‹የሚከፈላቸውን ገንዘብና ኑሮዋቸውን መመልከት ብቻ በቂ ነው፤›› ሲሉም አክለዋል፡፡

የሙስና ድርጊት በብድር አሰጣጥ ላይ እየተንሰራፋ ቢመጣም የብድር አሰጣጥ ሒደቱ መጓተት፣ የገንዘብ እጥረትና ተደራሽ አለመሆን ችግር የራሳቸው አስተዋፅኦ እንዳላቸው ይነገራል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተባለውን ችግር ለማጣራት እንደሚሞክርና መረጃ በተገኘባቸው ላይም ከበድ ያለ ዕርምጃ እንደሚወስድ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ የሥራ ኃላፊ ለሪፖርተር ገልጸው፣ ብሔራዊ ባንክ ግን የደኅንነት ሥራ መሥራት አይችልም ብለዋል፡፡

በየጊዜው ቅሬታዎች ለብሔራዊ ባንክ እንደሚቀርቡና መሰል የሙስና ድርጊቶች እየተለመዱ መሆናቸውን ገልጸው፣ በመሻሻል ላይ ባለው የባንክ ሥራዎች አዋጅ ብሔራዊ ባንክ የደኅንነት ሥራዎችን መሥራት እንዲችል ለማካተት እየተሞከረ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ይህ ዕውን ከሆነ እየተሰማ ያለው ችግር ሊፈታ እንደሚችልም አስረድተዋል፡፡

## በኢትዮጵያ መሰረተ ልማት ግልፀኝነት (In-frastructure Transparency) ላይ ትኩረት ያደረገ ስልጠና ተሰጠ





በኢትዮጵያ መሰረተ ልማት ግልፀኝነት) ላይ ትኩረት ያደረገ ስልጠና ለብሔራዊ ዘርፈ ብዙ ስራ አስፈጻሚ አባላት መሰጠት ተችሏል፡፡ ስልጠናዉ በዋናነት በመሰረተ ልማት ግልፀኝነት-ኢትዮጵያ (CoST-Ethiopia) ፕሮግራም ዋና ዋና ትኩረቶችና አሰራር፣ የፕሮጀክት መረጃ ለህዝብ ያለው ተደራሽነት፣ የመንግስት ግዥ ፈጻሚ አካላት እና የፕሮጀክት መረጃ ይፋ ማድረግ እንዲሁም ይፋ የተደረጉ የፕሮጀክት መረጃ ጥራት፣ ተገቢነትና፣ ታዓማኒነት በገለልተኛ ተቋም ማረጋገጥ ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑ ተገልጿል፡ እንዲሁም በመሰረተ ልማት ስራዎች ላይ የሚፈፀሙ ብልሹ አሰራሮችን በመለየት ችግሩን መፍታት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ግልፀኝነት መፍጥር እና ተጠያቂነትን በማስፈን መልካም አስተዳደር ማጎልበትን ዓላማ ያደረገ እንደሆነ ተመላክቷል፡፡

## በብልሹ አሠራር ጉዳያቸው የተጣራ 7 ሠራተኞች ከሥራ እንዲሰናበቱ 85 የሚሆኑት ደግሞ በዲሲፕሊን እንዲቀጡ ተደርጓል - የአዲስ አበባ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን

በብልሹ አሠራር ጉዳያቸው የተጣራ 7 ሠራተኞች ከሥራ እንዲሰናበቱ 85 የሚሆኑት ደግሞ በዲሲፕሊን እንዲቀጡ መደረጉን የአዲስ አበባ ደንብ ማስከበር ባለስሥጣን አስታወቀ፡፡ ባለፉት 9 ወራት 5 ሺህ 840 የመሬት ይዞታዎችን ከወረራ ማዳን ተችሏል ተብሏል፡፡ መሬት ባንክ ገብተው በተወረሩ 36 ይዞታዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ መደረጉን ያስታወቀው ባለሥልጣኑ፣ 6 ሺህ 515 የሕገ-ወጥ ግንባታዎች ላይ እርምጃ ተወስዷልም ብሏል፡፡
የ9 ወራት አፈፃፀሙን የገመገመው ባለሥልጣኑ ከደንብ ተላላፊዎች ቅጣት እና ከተወረሱ ንብረቶች 34 ሚሊዮን 873 ሺህ 563 ብር ገቢ መገኘቱን እና ከዚህም 34 ሚሊዮን 420 ሺህ 813 ብር ለፋይናንስ ገቢ መደረጉን አመልክቷል፡፡ ቀሪውን




ገንዘብ ገቢ ለማድረግ በማኅበራዊ ፍርድ ቤት በሂደት ላይ እንደሚገኝም መግለፁን አዲስ ሚዲያ ኔትወርክ ዘግቧል፡፡
በብልሹ አሠራር ጉዳያቸው የተጣራ 7 ሠራተኞች ከሥራ እንዲሰናበቱ 85 የሚሆኑት ደግሞ በዲሲፕሊን እንዲቀጡ ተደርጓልም ተብሏል፡፡ በነዚህ ወራት ሕገ ወጥ ንግድን እና የመሬት ሀብትን ከወራሪዎች በማዳን ረገድ ስኬታማ ሥራዎች መሠራታቸውንም በግምገማው ላይ ተነሥቷል፡፡

# የቬንዙዌላ የቀድሞ የነዳጅ ሚኒስትር ታሬክ ኤል አይሳሚ በሙስና ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር መዋላቸው ተገለፀ




የቬንዙዌላ የቀድሞ የነዳጅ ሚኒስቴር ሚኒስትር ታሬክ ኤል አይሳሚ በሙስና ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የሀገሪቱ መንግስት ገልጿል።

ታሬክ ኤል አይሳሚ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ከነዳጅ ሃብት መጥፋት ጋር ተያይዞ በተፈጠረ ክስ ምክኒያት ምርመራ እየተካሄደባቸው እንደሆነ ተገልጿል። በማጭበርበሩ ውስጥ ተሳትፈዋል የተባሉ ከ50 በላይ ሰዎችም መታሰራቸው ተገልጿል።

መንግስት ምን ያህል ገንዘብ እንዳጣ በትክክል ባይናገርም የቬንዙዌላ ጠቅላይ አቃቤ ህግ ግን ከህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር ጋር በተያያዘ የወንጀል ማህበሩን ጨምሮ ኤል አይሳሚን የመጀመሪያው ፍርድ ቤት እንደሚያቀርብ ገልጿል።

ኤል አይሳሚ ባለፈው አመት ከነዳጅ ሚኒስትርነቱ ባልተጠበቀ ሁኔታ መንግስት በሚመራው የድፍድፍ ኢንዱስትሪ ላይ በተካሄደው የሙስና ምርመራ ምክኒያት ስራ መልቀቁን አስታውሶ ሲጂቲኤን አሜሪካ ዘግቧል።

# 44 ቢሊየን ዶላር ያጭበረበረችው ቬትናማዊት ቱጃር በሞት እንድትቀጣ ተወሰነ



44 ቢሊየን ዶላር ያጭበረበረችው ቬትናማዊት ቢሊየነር በሞት እንድትቀጣ የሀገሪቱ ፍርድ ቤት ውሳኔ አሳለፈ፡

ትሩኦንግ ማይ የተባለችው የ67 ዓመት ቬትናማዊት ቱጃር ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በሀገሪቱ ከሚገኘው ሳይጎን የንግድ ባንክ ለ11 ዓመታት ያህል ዘረፋ ስትፈፅም እንደነበር ተገልጿል። ግለሰቧ ከመዘበረችው ገንዘብ ውስጥ 27 ቢሊየን ያህል ዶላር ተመላሽ እንድታደርግ ብይን ቢሰጥም፤ ዐቃቤ ህግ ግለሰቧ ገንዘቡን መመለስ እንደማትችል በማረጋገጡ የሞት ቅጣቱ እንደተላለፈባት ተመላክቷል።

ግለሰቧ የፈፀመችው ወንጀል ውስብስብ የወንጀል ድርጊት ሲሆን በአጠቃላይ 44 ቢሊዮን ዶላር ወይም 35 ቢሊዮን ዩሮ በመመዝበር የሞት ፍርድ የተፈረደባት የመጀምሪያዋ ቬትናማዊት ሆናለች ነው የተባለው። ቢሊየነሯ ትሩኦንግ ማይ በተለያዩ ሚስጢራዊ ኩባንያዎቿ የሸሸገችውን ሀብት በመጠቀም የወሰደችውን ገንዘብ የምትመልስ ከሆነ የሞት ፍርዱ ሊቀርላት እንደሚችል ተነግሯል። በግለሰቧ የክስ ሂደቱ 10 አቃቤ ህጎች እና 200 ጠበቆች መሳተፋቸው የተገለፀ ሲሆን 2 ሺህ 700 ምስክሮች ቃላቸውን እንዲሰጡ የጥሪ ወረቀት እንደደረሳቸውና ከ5 ሺህ 400 ኪሎግራም በላይ የሚመዝኑ የሰነድ ማስረጃዎች በ104 ሳጥኖች መቅረባቸውም ተገልጿል።

በቬትናም ታይቶ አይታወቅም በተባለው ግዙፍ የፍርድ ሂደት ከቢሊየነሯ ጋር 85 ሰዎችም ክስ ቀርቦባቸዋል መባሉን የዘጋርዲያን እና ቢቢሲ ዘገባዎች ያመለክታል።

# ኮሚሽኑ የስራ ከባቢን ምቹ ከማደረግ አንጻር አመረቂ ስራ አከናውኗል።

የሱፐርቪዥን ቡድኑ



የፕላን እና ልማት ሚኒስቴር የሱፐርቪዥን ቡድን የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የዘጠኝ ወራት አፈጻጸም ገምግሟል።

የሱፐርቪዥን ቡድኑ በኮሚሽኑ በመገኘት የተለያዩ የሥራ ክፍሎች የመስክ ምልከታ ያደረገ ሲሆን ከኮሚሽኑ ከፍተኛ አመራሮች ጋርም ውይይት አካሂዷል። ኮበውይይቱ የኮሚሽኑ የ9 አፈጻፀም ቀርቦ ውይይት ተካሂዶበታል። በውይይቱ ወቅት እንደተገለፀው ኮሚሽኑ የሥራ ከባቢን ምቹ በማድረግ ረገድ አመረቂ ስራ ማከናወኑ ተገልጧል።

ክቡር ወዶ አጦ የስነምግበር ዘርፍ ም/ኮሚሽነር እንደገለፁት ሀገሪቱ ያጋጠማት የሥነምግባር ስብራት የበርካታ ችግሮች ምንጭ በመሆኑ አጋር አካላት በከፍተኛ ትኩረት ሊሰሩ እንደሚገባ አመላክተዋል። ችግሩን ለመቅረፍ ኮሚሽኑ ዘረፍ ተኮር የሥነምግበር ስልጠና እና ግንዛቤ ማጎልበቻ ተግባራት እያከናወነ መሆኑን ጠቅሰው የመገናኛ ብዙኃን ሚናቸውን በአግባቡ ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል። ክቡር እሸቴ አስፋው የሙስና መከላከል ዘርፍ ም/ኮሚሽነር በበኩላቸው በአስቸኳይ መከላከል በረካታ የህዝብ ሃብት ማዳን መቻሉን ገልፀው በቀጣይ ልዩ ትኩረት በተደረገባቸው ዘርፎች ላይ የተጠናውን የሙሰና መከላከል ጥናት በማጠናቀቅ ወደ ተግባር ለመግባት ርብርብ እንደሚደረግ አስገንዝበዋል። የሱፐርቪዥን ቡድኑ የሥነምግባር ግንባታን በሰፊው ከማከናወን አንጻር እንዲሁም የተለዕኮ ተግባራትን በቅንጅት ከመስራት አኳያ በቀጣይ ትኩረት መደረግ እንዳለበት አመላክቷል።

ከዚሁ በተጨማሪ የጥቆማ ስርዓትን ደህንነት ማስጠበቅ ከሀገሪቱ አጠቃላይ ለውጥ ጋር የተሰናሰለ የሙስና መከላከል አሰራር ስርዓት መታሰብ እንዳለበት ጠቁመዋል።



# ርዕሰ-አንቀፅ

## ለውጤታማ የፀረ-ሙስና ትግል የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ፖሊሲ አስፈላጊ ነው!

ሙስና በሀገራችን የልማት፣ የእድገትና የሰላም ችግር ነው፤ በሁሉም ተቋማትና ግለሰቦች ሊሠራ የሚችል ነው፡፡ ለዚህም በፌዴራል፣ በክልልና በከተማ አስተዳደር ደረጃ የፀረ-ሙስና ተቋማት ተደራጅተው በትውልድ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሥራ ላይ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከማስተማርና ከመከላከል ሥራ በተጨማሪ የፌደራል ፖሊስና የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ወንጀል ላይ ህግ ማስከበር ሥራ እየሠሩ ናቸው፡፡

በተቋማት ውስጥ የክትትልና የቁጥጥር ሚና ያለቸው የውስጥ አዲት፣ የለውጥና መልካም አስተዳደር፣ የህግ አገልግሎት እንዲሁም የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ቢኖሩም ተቀንጅተው ስለማይሰሩ ሙስናን የመከላከል ሚናቸውን በተገቢ እየተወጡ አይደለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የዋና አዲት መሥሪያ ቤት፣ የገንዘብ ሚኒስቴር የኢንስፔክሽን መምሪያ፣ የኦዲት አገልግሎት መሥሪያ ቤት፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተደርጅቶ የክትትልና የቁጥጥር ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛሉ፡፡ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ላይ መፍትሄ የሚያፈላልግ የህዝብ እንባ ጠበቂ ተቋም እንዲሁም የዜጎች ሰብኣዊ ጉዳዮችን የሚመለከት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ተደራጅቷል፡፡ እነዚህ በርካታ የክትትልና ቁጥጥር አደረጃጀቶች ቢኖሩም በሀገራችን ሙስና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባበሰ እንጅ እየቀነሰ አይታይም፡፡

በሀገራችን በርካታ መልካም የማህበረሰብ እሴቶች እያሉ እነዚህ እሴቶች እየተሸረሸሩ ስግብግብነትና ራስ ወዳድነት እያየለ በመምጣቱ የመንግስት አገልግሎቶችን ያለእጅ መንሻ በማይገኝበት ደረጃ ላይ እየተደረሰ ነው፡፡ ከፍተኛ ገንዘብ የሚፈስባቸው የመንግስት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችም በሙስና እና ብልሹ አሰራር ምክኒያት በተያዘላቸው ጊዜ እየተጠናቀቁ አይደለም፡፡ ከተያዘላቸው በጀት በላይ ወጪ ይጠይቃሉ፣ ቢጠናቀቁም የጥራት ጉድለት ስለሚኖርባቸው ለሌላ ወጪ ሲዳረጉ ወይም ለህዝብ ተጠቃሚነት ሳይውሉ የሚቀርቡት ሁኔታዎች ይስተዋላል፡፡

በመሆኑም ይህን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በየጊዜው አዳዲስ አሰራሮችን መዘርጋትና መተግባር የግድ ይላል፡፡ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ፖሊሲ ማዘጋጀትና መተግበር የፀረ-ሙስና ትግል ህዝባዊነት እንዲኖረው ከማድረግ በተጨማሪ በፀረ-ሙስና ትግሉ ላይ ሚና የሚኖራቸው የባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ግዴታ እንዲወጡ ለማድረግ ያስችላል፡፡

ስለሆነም ፖሊሰው ቅድሚያ የሚሰጠው በትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ላይ ነው፡፡ የሥነምግባር ግንባታ የሚጀምረው ከቤተሰብ ስለሆነ ወላጆች ልጆቻውን በመልካም ሥነምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚጠበቅባቸው ሚና በተገቢ እንዲወጡ ፖሊሲው ግልፅ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

ማህበረሰብ ያለቸውን መልካም እሴቶችን በማዳበር በሥነምግባር የታነፀ ማህበረሰብ ማብዛት ላይ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡ ተቋማት ያሉባቸውን የውስጥ ችግሮችን በሪፎርም ሥራ በማስተካከል በሥነምግባር የተገነባ አመራርና ሠራተኛ ማፍራትና መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል የሙስና መከላከል ሥራን ተቋማዊ ማድረግ ለትግሉ ባለቤትነትን ሊፈጥር ይችላል፡፡ በዚህም ተቋማት ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ቀዳደ የሚከፍቱ አሠራሮችን በጥናት በመለየት የመከላከያ ስትራቴጂ መንደፍና እንዲተገብሩ ማድረግን ፖሊሲው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

በሙስና የተመዘበረ ሀብት ማስመለስ ሥራ ወጥነት ያለው አሠራር ከመዘርጋቱም ሌላ በውጤታማነት የሚተገበር አይደለም፤ ስለሆነም ይህን ችግር በዛለቂነት ለመፍታት የሚያስችል አሠራር ፖሊሲው ሊዳሰስ ይገባል፡፡

የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ፖሊሰው የፀረ-ሙስና ትግሉን ህዝባዊ ከማድረግ ባሻገር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሚና የሚኖራቸው ዘርፎችና ተቋማት በምን አግባብ ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለበቸው አቅጣጫዎችን የሚያስቀምጥ እንዲሆን ፖሊሲው በኮሚሽኑ ተዘጋጅቶ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ ከመደረጉ በፊት ፖሊሲው ሚና ካለቸው የባለድርሻ አካላት የፀረ-ሙስና ተቋማት አመራርና ሠራተኞች፣ ምሁራን፣ የሲቪል ማህበረሰብ፣ ሚዲያዎች፣ የግል ዘርፍ፣ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ወዘተ በረቂቅ ፖሊሲው ላይ ሰፊ ውይይትና ክርክር ይደረግበታል፡፡

በመሆኑም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የተዘጋጀው የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፖሊሲ ህዝባዊ መሠረት ኖሮት ውጤታማ የፀረ-ሙስና ትግል በማካሄድ ሀገራችን የልማትና እድገት ጉዞን ለማፈጣን ከፍተኛ እገዛ እንዲያደርግ የድርሻቸውን መወጣትና አስፈላጊ ግብዓቶችንና አስተያየቶችን መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡






# ቆይታ



## “በከተሞች የሚሰሩ መሰረተ ልማቶች ተረክቦ የሚያስቀጥል በስነምግባር የታነጸ ትዉልድ ያስፈልጋል”!

ሊቀ ትጉኃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ

ቆይታ የትውልድን ሥነምግባር ለመገንባትና ሙስናን ለመከላከል የሚያስችሉ ርዕሰ ጉዳዮችን እያነሳ ከተለያዩ ግለሰቦች ጋር የሀሳብ ልውውጥ የሚያደርግበት አምድ ሲሆን ፀረ-ሙስና ጋዜጣም በመጋቢት ወር እትሙ ትውልዱ በመልካም ስነምግባር እንዲታነጽ በተለይም ለህጻናት እና ወጣቶች ተምሳሌት ከሆኑት ሊቀ ትጉኃ ቀሲስ ታጋይ ታደለ ጋር የሚከተለውን ቆይታ አድርጓል፡፡



ፀረሙስና ጋዜጣ፡- በሀገራችን በተለይም በወጣቶች ላይ በሰፊው እየታየ የመጣው የሥነምግባር ጉድለት መንስኤው ምንድን ነው? ምንስ መደረግ አለበት ይላሉ?

ቀሲስ ታጋይ፡- ለአንድ ሃገር መሰረቱ ትውልድ ነው፡፡ ሀገር ተገነባ የሚባለዉ ትውልዱን መገንባት ሲቻል ነው፡፡ የሀገር ግንባታ ቀጣይነት ግባችን ጎላችን በትውልድ ላይ ትውልዳዊ አሻራዎች ናቸው፡፡ ለዚህም ማሳያ የምንለዉ ቀጣይነት ያለዉ ግቦች ትውልድ ላይ የሆነ እምርታ ማምጣት ስንችል ነዉ፡፡ በስነምግባር ግብረገብነት የቀረፅነው ትውልድ አብቦና አፍርቶ ፍሬ ማሳየት ሲጀምር አንድን ሃገር በትክክል ይገነባል ማለት ነው፡

ከተሞች ላይ የተለያዩ መሰረተ ልማቶች ሊገነቡ ይችላሉ፡፡ ተረክቦ የሚያስቀጥል ትዉልድ ከሌለ በሆነ ወቅት ላይ ይፈርሳል፡፡ ይህንን የሚያስቀጥል ትውልድም አይኖርም ለምሳሌ አባይ የተጀመረው በሌላ ትውልድ ይሆናል የሚያስቀጥለዉና የሚረከበው ሌላ ትዉልድ ይሆናል፡፡ የገነባው ሌላ ትውልድ ነው አክሱም እና ላሊበላ የምንላቸው የገነቧቸዉ ሌሎች ናቸዉ፡፡ ያንን ግን ተረክቦ ታሪካቸዉ እንዲቀጥል የሚያደርገዉ ደግሞ ሌላዉ ትውልድ ይሆናል፡፡ ትዉልድ ተገነባ ብለን መናገር የምንችለው ቀጣይነት ሲኖረዉ ነው፡፡በሥነምግባር የተገነባ ትውልድ ከሌለ፤ ለዘመናት የተገነባን ከተማ ሊያፈርሰው ይችላል፡፡ በመልካም ሥነምግባር የታነፀ ትውልድ ከሌለ ሀገሮች ከተሞች ይፈርሳሉ፤ እርስ በርስ ወደ መበላላት ይሄዳል፡፡ ስለዚህ ትውልድ ላይ መስራት አለብን

ትውልዱን በተለይም ህጻናትና ወጣቶችን በሥነምግባር ለመገንባት የተለያዩ አካላት ኃላፊነት ሊወስዱ ይገባል፡፡ ህጻናትና ወጣቶችን በሥነምግባር ለመገንባት አራት አካላት ሃላፊነት አለባቸው፡፡ 1ኛ. የመጀመሪያው ወላጆች/ቤተስብ ናቸው፡፡ ቤተሰብ/ወላጆች ሥነምግባርን በማስረፅ አኳያ ልጆች የት ዋሉ፤ ምን ተማሩ፤ ምን ይዘዉ መጡ፤ ምን እያረጉ ነው፤ ወደፊትስ ምንድነዉ እጣፈንታቸው የሚለውን ነገር ትዉልዱን የማነፅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ልጅ ችግኝ ነው እናትና አባት ልጆቻቸውን ከመኮትኮት ጀምሮ ችግኙን ውሃ እያጠጣ ማዳበሪያ እያረግን አፈር እያሳቀፍን እየተንከባከብን እንደምናሳደግ ሁሉ ልጆችንም ለማሳደግ የመጀሪያው ሀላፊነት ያለበት ቤተሰብ ወይም ወላጅ ነው፡፡

2ኛ. ሁለተኛው ልጆችን የሚንከባከቡት ትምህርት ቤቶች ናቸዉ፡፡ ከወላጆች ተረክቦ እንደ ወላጆች ከሁለት ሰዓት አንስቶ ልጆችን የመንከባከቡት ስራ የመምህራን ነው፡፡ ልጆችን ከህፃንነት አንስቶ ፊትፍተው የሚመግቡት እና የሚያሳድጉት መምህራን ናቸው፡፡ ለዚህም መምህራን የጥውልዱን ሥነምግባር ለመገንባት ሁለተኛውን ኃላፊነት ይወስዳሉ፡፡

3ኛ. ሶስተኛዉ ደግሞ ቤተዕምት/የሀይማኖት ተቋማት ናቸው፡፡ በሰንደይ ስኩል ከ11 ሠዓት ጀምሮ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ ልጆችን የሚያስተምሩት ቤተ እምነቶች ናቸዉ፡፡ ቤተዕምት/የሀይማኖት ኃላፊነቱን በሶስተኛ ደረጃ ይወስዳሉ፡፡ ስለዚህ ብዙ ዜጎች ናቸዉ ኃላፊነቱን መዉሰድ ያለባቸዉ፡፡ ስለዚህ የእምነት ተቋማት ልጆችን በሥነምግባር የማነፅ የማስተካከል በጎዉን ከክፉ እንዲለዩ ከማድረግ፣ የሰማይ ቤታቸዉን እንዲያስቡ ከማድረግ፣ ምድራዊ ጠፊ ኃላፊ በሆነ ነገር እናዳይታለሉ ማደረግ፣ እናት አባቶቻቸዉን እንዲያከብሩ ማድረግ፣ ይህንን በማድረጋቸዉ በምድር ላይ እድሜያቸዉ እንደሚረዝም የማስተምሩ ኃላፊነት የእነሱ ነው፡፡ ስለዚህ ቤተ እምነቶች ልጆቸን ከመንከባከብ ረገድ ከፈጣሪ ተሰጥቷቸዋል፡፡

4ኛ. አራተኛውና የመጨረሻዉ ደግሞ መንግስት ነው፡፡ ትውልዱ አልባሌ ቦታ እናዳያርፉ በጥሩ መንገድ እንዲሄድ በካሬኩለም፤ በመመሪያ በህግ፤ በደንብ የመጠበቅ የልጆች ከለላ ሆኖ መብታቸውን እና ግዴታቸዉን እንዲያዉቁ ፖሊሲ አውጭ የሀገር አስተዳዳሪ ኃላፊነት ይሆናል፡፡ እነዚህ አራቱ አካላት ተሰናስለዉ፣ ተናበዉና ተሰባጥረው፡ ቤተ እምነቶች ከእናት አባት ት/ቤቶች ከወላጅ መምህራን ከመንግስታት ጋራ አብረዉ እጅና ጓንት ሆነው ተናበው ትውልዱ ላይ ኢንቨስት ማድርግ አለባቸዉ፡፡ እነዚህ አራቱ አካላት አንዱ ፊል ካደረገ ቤተሰብ የገነባውን ትምህርት ቤት የሚያፈርስ ከሆነ ትምህርት ቤት የገነባዉን ቤተ እምነቶች የሚያፈርሱ ከሆነ ቤተ እምነቶች የገነቡትን መንግስት የሚያፈርስ ከሆነ ተጠያቂው አፍራሽ አካል ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ በአንድ ላይ ትውልዱ ላይ ኢቨስት ማድረግ አለባቸዉ እላለሁ፡፡

እነዚህ አራቱ አካላት ቁጭ ብለዉ ተናበዉ መንግስትም ለትምህርት ተቋማት ካሬኩለም እንዲቀርፅ በሥነምግባርና በግብረ-ገብነት ትምህርት እንዲዘጋጅላቸዉ፤ቤተ እምነቶች ልጆች ተጫዉተዉ ብቻ እንዲሄዱ ሳይሆን የነገዋ ኢትዮጵያን በማሰብ ሰማያዊ ገነት መንግስተ ሰማያትን እያሰቡ የነጋቸዉን ልጆች ወልደው አሳድገዉ እንዲኖሩ በማድረግ ኃላፊነት ከማድርግ አኳያ እነዚህ አራቱ አካላት ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ለእድገታቸውም ለጥፋታቸውም ለመሰደዳቸውም ተጠያቂዎች እነዚህ ናቸዉ፡፡

ፀረሙስና ጋዜጣ፡- በእመነት ተቋማት የትውልዱን ሥነምግባርን በተጨባጭ ለመገንባት ምን እየተሰራ ነው?

ቀሲስ ታጋይ፡- ኢትዮጵያ የኃይማኖት ሀገር ነች 97/98 በመቶ የሚሆነዉ ህዝብ ሀይማኖተኛ ነዉ፡፡ ወይ ክርስቲያን ነዉ ወይ ሙስሊም ነዉ፡፡ መሬት ላይ ግን ሀይማኖቶቹ አሉ ወይ ብልን ብንጠይቅ አጠያያቂ ነዉ የሚሆነዉ፡፡ ቸር እረኛ አለ በአንድ አውድማ ላይ በአንድ መሬት ላይ አንደኛ እረኛ ከሆነ ገና በቅርብ ነዉ ከብቶቹን የሚመልሳቸው በሰዓቱ ዉሓ ያጠጣቸዋል ከተለያየ ነገር ይከላከላቸዋል አውሬም ቢመጣ ይታደጋቸዋል፡፡ ምንደኛ ከሆነ ደግሞ ተኝቶ አንቀላፍቶ ዝናብ ቢመጣ የማይከላከላቸዉ አውሬም ቢመጣ የማይከላከላቸዉ ከሆነ እሱ ምንደኛ ነዉ፡፡ ትዉልዱ ላይ እንደዛ ነዉ መልካም እረኛ አለ መልካም አባት መልካም መምህር ልጆቹን ለነገ ብሎ ይታደጋል ምን አገባኝ የሚል ከሆነ ደግሞ እሱ ምንደኛ ነዉ፡፡

ሌባ ቢሆን ማጅራት መቺ ቋንጃ ሰባሪ ደም አፍሳሽ ምናገባኝ የሚል ከሆነ አስቸጋሪ ነው፡፡ ዉጭ ሐገር ሲኬድ ቆሻሻ መጣል በየ መንገዱ መፀዳዳት ክልክል ነዉ፡፡ ወደ ሀገራችንም እየተጀመሩ ነዉ፡፡ ይህንን ባህል እየቀየርክ የምትመጣ አንተ ነህ

ትኩረት ተሰጥቶበት ፅዱ ለኑሮ ተስማሚ ይሆናል። ትዉልዱ ላይ ውጤት ለማምጣት ልጆች ላይ ከተሰራህ ውጤት እናመጣለን። ትዉልዱ ላይ ለውጥ ይመጣል። ያለፈው ትውልድ አልፏል መጭው ትውልድ ላይ ግን መስራት እንችላለን። ሁለተኛ ትውልድ ቤተ እምነቶች የመምከር የማስተማር ትልቁ ኃላፊነት ያለው ቤተ እምነት ላይ ነዉ። ኃይማኖት ተቋማት የኃይማኖት ሀገር ነን በትክክል እኛ ስልጣናችንን መሬት ላይ ማዉረድ ከቻልን እና ህዝቡ ላይ መስራት ከቻልን በርግጠኝነት የሚሰማን አሁን ነው። ምንደኛ ሆነን በትክክል በዚህ ላይ መስራት ካልቻልን በአንድም በሌላም ይህ ኃይማኖተኛ ትውልድ ነዉ አሁን ማጅራት መች ቋንጃ ሰባሪ ፤አፈናቃይ፤ጦረኛ ፤ዘረኛ፤ሌባ ሆኖ የምናየዉ ዞሮዞሮ የኛዉ ክርስቲያን ወይ ሙስሊም ነው። ከአዉሮፓ ወይ ከሌላ አልመጣም ምናልባት ሀሳቡ ከዛ የመጣ ይሆናል ሰዎቹ ግን እዚሁ የእኛው ልጆች ናቸው።

ስለዚህ እኛ ትዉልድ ላይ እንስራ የታነፀ ትዉልድ ካለ ሀገር ያንፃል የታነፀ አዕምሮ ካለ ሀገር ይገነባል።

**ፀረሙስና ጋዜጣ፡-** ትውልዱ ግብረ-ገብ ያለው እንዲሆን እና ሀገሩን እንዲወድ ከሀይማኖት አባቶችና ከእመነት ተከታዮ ምን ይጠበቃል ይላሉ?

**ቀሲስ ታጋይ፡-** ቤተ እምነቶች በተለይ ትዉልዱ ላይ እስካሁን ከሰራነዉ ይበልጥ መስራት አለብን። ሥነምግባር ላይ የትምህርት ተቋማት መስራት አለባቸዉ። ግብረገብ ትምህርት ተብሎ በንጉሱ ዘመን እንደነበረዉ አንዳንዱን በጎ ነገር ዛሬ ላይ ማምጣት ይቻላል። ለሀገሩ መሪ ያላቸዉ ክብር ልዩ ነበር። አሁን ላይ ግን መሪዉን የሚያንቋሽሽ ትዉልድ ፈጥረናል። መሪዊን ይገደል የሚል ትዉልድ ፈጥረናል። አንዳንድ ጥሩ ጥሩ ነገሮችንም መዉሰድ/መቅዳት አለብን። ትዉልዱ መሪዉን የሚያከብረዉ ጥይት ተደርጎበት አይደለም ሲያከብሩ አይቶ ነው።

የትዉልድ ጋፓ ተፈጥሮብናል እኛ ክፍተቱን ወስደነዋል። አሁን ግን መስራ አለብን ብልን በሰንበት ትምህርት አስተምሮአቸዉ ዓርብ ጁምዓ ላይ ኢማሞቹ እንዲሰሩ የማድረግ ስራ እየሰራን ነዉ። ምናልባት ዉጤቱ ዛሬ ላይ ላይሆን ይችላል። ትዉልድ ላይ እየሰራን ስለሆነ ያንን ፍሬ እየወሰድን ዛሬዉኑ ዘርተን ዛሬዉኑ ፍሬ አንጠብቅም። ትዉልድ ቅብብሎሽ ነዉ፤ የትዉልድ ስራ ተሸጋጋሪ ነዉ መቆም የለበትም ይህንን በቀጣይነት መስራት አለብን።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** የሙስና መስፋፋት መንስኤው ምንድንነው ምንስ መደረግ አለበት ይላሉ?

**ቀሲስ ታጋይ ታደለ፡-** ሙስና መጀመሪያ ጉቦ መማላጃ ይኸን ነገር ከፈፀምክልኝ ይህን ላድርግልህ አይነት እሳቤ ያለው ነው። በነጻ የተቀበላችሁትን በነፃ ስጡ ይላል መጽሀፍ። ዛሬ እዉቀት ሊኖር ይችላል ወቅትና ጊዜ ፈቅዶልህ ይሆናል አንዳንዴም እድል ሰጥቶህ ስልጣን አግኝተህ ይሆናል ሀብት አግኝተህ ይሆናል። በዚህ ውስጥ ሰጭዉም ተቀባዩም ሌቦች ናቸዉ። ጉቦ ለማግኘት ከመጓጓት እና ጥቅሙን ለማስቀደም ነው ሙስና የሚመጣው። ሌብነት ብዙ ነገር ይጎዳል ዉስጣዊ ጉዳት ከእግዚአብሄር ዘንድ ትጠየቃለህ።

በውሸት የሚመጣ ነገር ጉዳት ያስከትላል። ሌብነትና ሙስና አጭበርብረህ ዋሽተህ ቀጥፈህ አታለህ መማለጃ አድርገህ በአቋራጭ ለመበልፀግ የሚደረግ ሩጫ ነው። የሆነ ነገር ሰጥተህ የሆነ ነገር ለማግኘት ነዉ የሰዉን የድሆችን የህዝብን ሀብት ለመበልጸጊያነት ነዉ። አንድ ሰጥቶ ሁለት ለማግኘት ነዉ።

ጎቦ መማለጃ የምንለዉ በመጽሀፍ ቅዱስ መንቀዝ ነዉ፤ መበላሸት ነዉ። ሆኖም ጉቦ ተቀባዩም ሆነ ሰጪው በሰማይ ይጠየቃል በምድርም ይጠየቃል። ምድር ሲገኝበት በፀረ-መስናም ሆነ በፖሊስ ሲደረስበት የጊዜ ጉዳይ እንጂ ይጠየቃል። በሰማይ ደግሞ ህሊናዉም ይጠይቀዋል እግዚአብሔር ይጠይቀዋል። በራስህ በላብህ በወዝህ ጥረህ ግረህ ብላ ነዉ የሚለዉ። ደመወዝህ ይበቃሀል ነዉ የሚለዉ የሌላ አትመኝ ከስርዓት ያፈነገጠ ኃይመኖታዊ አስተምህሮ የሌለዉ ከፈጣሪም ዘንድ የሚያስጠይቀዉ በምድርም በወንጀል የሚጠየቅበት ነዉ ማለት ነዉ።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ይህ ድርጊት በኃይማኖት አባቶች ሲሆን ያስጠላል። አርዓያ ሞዴል መሆን የሚገባን ደግሞ መምሬ እገሌ እንደዚህ ሆኖ ሼህ እገሌ እንደዚህ ሆኖ ፓስተር እገሌ እንደዚህ ሆኖ እሱ እንደዚህ እየሄደ እኛን የሚያጣቅሱን ለመስረቅ ለሌብነት ለወንጀል እኛን እንደ ምሳሌ ይጠቀሙብናል። እኛ በስነምግባር አርአያ ሆነን እሳቸዉ እንደዚህ ሆነዉ እግዚአብሔር ጠብቋቸዋል ሊሉን ይገባል። እሳቸው ሰርቀው ቤት ሰርተዉ ከተባልን ጥሩ አይደለም እና በተለይ የሀገር መሪ የጎሳ መሪ ራሳችንን መጠበቅ አለብን። እሱ ሌባ ከሆነ ትዉልዱን ለማስተማር ሰሚ የለዉም ሞራል የለዉም ሞራል የሚኖረዉ ራሱን ነፃ አዉጥቶ ህዝቡን ነፃ አዉጥቶ ለመኖር ሲጥር ብቻ ነዉ።

ስለሆነም በየደረጃወ ያሉ የሀይማኖት አባቶችና የመንግስት ባለስልጣን አካላት አርአያ ሆነዉ ለትውልዱ ሥነምግባር ግንባታ የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ ይገባል። እንግዲህ ትዉልድ ቅብብሎሽ ነዉ የሆነ ትዉልድ ነበረ ዛሬ ያለነዉ እኛ ነን ነገ ደግሞ ሌላዉ ትዉልድ እየመጣ ነዉ።

**ፀረሙስና ጋዜጣ፡-** ህጻናትና ወጣቶች በስነምግባር ታንጸው ሌብነትን እንዲጸየፉ ለህጻናትና ወጣቶች ምን መልዕክት ያስተላልፋሉ?

**ቀሲስ ታጋይ ታደለ፡-** ባህልን ቅርስን ሀብትን የሚረከበዉ ትዉልድ ነዉ። ለዚህ ደግሞ ሳናቀማማ ሳንገፋፋ መሄድ አለብን። የትዉልድ ቅብብሎሽ በሂደት እንጂ በሆነ በአቋራጮች እንዳልሆነ እመክራለሁ ።

ትዉልዱ ይህንን አዉቆ ተረድቶ እግዚአብሄር የሰጠንን በማመስገን ወላጆችን፤ መሪዎች ማክበር፤ ሌብነትን መተዉ፤ ክፋትን መጠየፍ፤ ተንኮልን መጠየፍ ሸርን መተዉ በጎነትን ፤ ፍቅርን፤ትህትናን መላበስ ከትዉልዱ የሚጠበቅ ነዉ። ይህንን ብታደርጉ በምድር ላይ ዘመናችሁ ይረዝማል እድሜያችሁ ይረዝማል። ይህንን ባታደርግ ግን ትቀሰፋለህ ጠሪህ አይታወቅም በእንቅፋት፤በትንታ፤ በኤሌክትሪክ፤ በመኪና አደጋ ትሞታለህ ዛሬ ወጣት ነኝ የምትልበት ጊዜ አይደለም። በአጠቃላይ ይህንን ነዉ የምመክረዉ በጎ ዘመን እንዲመጣልን ክፉ ዘመን እንዲያርቅልን ነዉ።


## ፀረ-ሙስና

በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

| | |
|---|---|
| ስልክ | 011552-77-79 |
| ፖ.ሳ.ቁ | 34799 |
| ኢ-ሜይል | FeaccEthiopia2013@et |
| ድረ-ገጽ | www.feacc.gov.et |
| ፌስቡክ | www.facebook.com/feaccOfficial |
| ቴሌግራም | t.me/feacc |
| ትዊተር | www.twitter.com/EthiopiaFeacc |
| ዩቲዩብ | Federal Ethics & Anti-Corruption Commission |

ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች
www.feaccdars.gov.et

ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

| | |
|---|---|
| ስልክ | 011552 77-92/ 011553-38-52 |
| ሞባይል | 0935947533 |
| ፖ.ሳ.ቁ | 34799 |
| ድረ-ገጽ | www.feacc.gov.et |
| ኢ-ሜይል | CorruptionReportEthiopia@feacc. gov.et |
| ቴሌግራም | t.me/CorruptionPointing |
| ዋትስአፕ | wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1 |

# ሳ ይቃጠል በቅጠል

## በዕለት ደራሽ የዕርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት በግዥ አፈጻጸም ሂደት የሚታዩ ክፍተቶች

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ውስጥ የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶችን ለመዝጋት የችግሮችና መንስኤዎች በጥናት በመለየት ለሚመለከተው ተቋም የመፍትሄ ሃሳብ ማቅረብና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ከሚጠቀምባቸው ስልቶች አንዱ ነው፡ ይህ ፅሁፍ ኮሚሽኑ በተለይ በዕለት ደራሽ የዕርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት በግዥ አፈጻጸም ሂደት የሚታዩት ክፍተቶችን ለመለየት ባካሄደው የአስቸኳይ የሙስና ጥናት ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ በጥናቱ የተገኙ ውጤቶችን እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

የዕለት ደራሽ በተባለ የመንግስት የልማት ድርጅት ለ100 የከባድ መኪኖች ሸራ ለመግዛት በመወሰን የመንግስትንና የራሱን የደርጅቱን የግዥ አዋጅና መመሪያ በጣሰ ሁኔታ ብቸኛ አቅራቢ መሆኑ ካልተረጋገጠ “OMR Import Export” የተሰኘ የግል ድርጅት ጋር ያለምንም ግልፅ ጨረታ ውድድር ድርጅቱ በግል ባቀረበው ጥያቄ መነሻነት የ17 ሚሊዮን ብር የከባድ መኪና ሸራ ግዥ በመፈፀም ሂደት ላይ መሆኑን አስመልክቶ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ድርጊት እየተፈፀመ መሆኑን በደረሰ ጥቆማ መሰረት በተቋሙ በመገኘት ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ሰነዶችና መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመመልከት እና ከግዥና ፋይናንስ ክፍል ኃላፊዎች ጋር ውይይት በማድረግ ጥናቱ ተካሄዷል፡፡

በዚህም የዕለት ደራሽ የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት የግዥ መመሪያዎች፣ OMR Import & Export የድርጅት ፕሮፋይል፣ በኃይማኖት በቀለ እሽቱ ንግድ ስም በንግድ ፈቃድ ቁጥር BL/AA/14/673/221316/2014 BQNE 11/2/2014 በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የተሰጠ፣ ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች እና የኬሚካል ውጤቶች አስመጪነት ጥሬ ጎማ፣ ፕላስቲክ፣ ባትሪ እና ውጤቶቻቸው አስመጪነት የሚገልፅ ሰነድ፣ በDec 7,2023 በመንግስት የግዥ ባለስልጣን ዌብ ሳይት የኢጂፕ መረጃ ላይ OMR Import & Export (ኃይማኖት በቀለ) የተባለው ድርጅት sole proprietorship መሆናቸውን የሚገልፅ ስነድ አጥኝዎች ተመልክተዋል፡

እንዲሁም በ03/25/2016 የተፃፈ የማኔጅመንት ስብሰባ ቃለ ጉባኤ በመንግስት የግዥ ባለስልጣን ዌብ ሳይት የኢጂፕ እና ድርጅቱ ካለበት የገንዘብ ዕዳ፣ እጥረት በተጨማሪ ከምርቱ ጥራት ድርጅቱ ሊያገኝ ከሚችለው ጠቀሜታ አሸናፊው ድርጅት ባቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ መሰረት ግዥው እንዲፈፀም የቀረበ የውሳኔ ኃሳብ እና የቴክኒክ ግምገማ ሰነድ፣ በ15/04/2016 የተፃፈ የቅድመ ክፍያ ማስከበሪያ ሰነድ እና የከባድ ተሽከርካሪ የፕላስቲክ ሸራ ግዥ የውል ሰነድ እንዲሁም ድርጅቱ ከማኔጅመንት ውሳኔ ተነስቶ ግዥው እንዲፈቀድ ለቦርዱ የፃፈው ደብዳቤ መመልከት ተችሏል፡፡

የዕለት ደራሽ የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ግዥ ክፍል ለ100 ከባድ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውል የፕላስቲክ ሸራ ግዥ ለመፈፀም መንግስታዊ ከሆኑ ድርጅቶች ለመከላከያ ሰራዊት ፋዉንዴሽን አዳማ ጋርመንት ጥያቄ ሲያቀርብ፣ አዳማ ጋርመንት ኢንዱስትሪ ማምረት እንዳቆመ መግለፁን ከውይይትና ከማኔጅመንቱ ውሳኔ ቃለጉባኤ ተመላክቷል፡፡ አጥኚው ቡድን የዕለት ደራሽ የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ምንም አይነት በመንግስትና በድርጅቱ የግዥ መመሪያዎች የተደነገጉ የግዥ መፈፀሚያ መንገዶችን ግልፅ የጨረታ ሂደትን ባልተከተለ ሁኔታ “OMR” የተባለ አስመጪ ድርጅት በራሱ ፍቃድ የተፈለገውን ሸራ ለማቅረብ የጠየቀ መሆኑና ይኸው ተፈቅዶለት ጥራቱን የሚያረጋግጥ የቴክኒክ ቡድን በድርጅቱ ኃላፊ የተቋቋመ መሆኑ፣ የተቋቋመው የቴክኒካል ኮሚቴ በቀን 06/03/2016 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ OMR Import & Export ድርጅት ለሌሎች ሀገር በቀል ትራንስፖርት ድርጅቶች ጥቁር ዓባይ ትራንስፖርት አክሲዮን ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ለትራንስ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎች ሸያጭ መፈፀሙን አረጋግጧል

በሂደቱም የጥራት ሁኔታ፣ የአገልግሎት ጊዜውን እንዲሁም እነዚሁ ድርጅቶች የነበራቸዉን የግዥ ውልና የግዥ ዘዴ ያሰባሰበ መሆኑ፣ OMR Import & Export ድርጅት ደረጃውን የጠበቀ ጥራት ያለዉ የከባድ መኪና የፕላስቲክ ሸራ እንደሚያቀርብ ለድርጅቱ ማኔጅመንት በአካል በመገኘት በፀሑፍና በአካል በመገኘት ገለፃ ተደርጓል፡፡

እንዲሁም በ03/03/2016 ቁጥር አቅ/ፋ/ማ/0262/16 በተፃፈ ደብዳቤ ስፐላ ክሬዲት ሲስተም ግዥ ለተፈፀመላቸዉ 100 ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚዉል የፕላስቲክ ሸራ ከOMR Import & Export ድርጅት ግዥ እንዲፈፀም የዕለት ደራሽ የትራንስፖርት ድርጅት ማኔጅመንት ለዋና ዳይሬክተር ጥያቄ የቀረበ መሆኑ፣ በድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር በተቋቋመዉ ቴክኒካል ኮሚቴ በቀረበዉ

**የግዥው ሂደት ተቋርጦ አሳታፊ በሆነ መንገድ በግልፅ ጨረታ እንዲፈፀም ማድረግ ይገባል፡፡**

ውሳኔ ሀሳብ እና ከኢፌዲሪ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ድረ-ገፅ በተገኘዉ መረጃ መሰረት ብቸኛ አቅራቢ ነው በሚል OMR Import & Export ድርጅት ቀጥታ ግዥ እንዲፈፀም ማኔጅመንቱ የወሰነ መመልከት ተችሏል። በዕለት ደራሽ የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት በማጣራት ሂደቱም ውጤቶች የተገኙ ሲሆን፥ በድርጅቱ እየተካሄደ ያለዉ የሸራ ግዥ አስቸኳይ ነዉ በሚል ምክንያት በበላይ ኃላፊ እና በማኔጅመንት ዉሳኔ መሰረት ግልፅ ጨረታ ሳይወጣ ቀጥታ ከOMR Import & Export ድርጅት ግዥ የተፈፀመ መሆኑ፣ OMR Import Export የተባለው አስመጪ ድርጅት sole proprietorship በመሆን በኢፌዲሪ የመንግስት ግዥ እና ንብረት ባለስልጣን ድህረ ገፅ ላይ PVC TARPAULIN የፕላስቲክ ዕቃ ብቸኛ አቅራቢ ነው ይባል እንጂ ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በተገኘው መረጃ መሰረት ድርጅቱ ብቸኛ አቅራቢ አለመሆኑን የሚያስረዳ ነው። በተጨማሪም የማኔጅመንት ኮሚቴው ድርጅቱ እንዲያቀርብ ሲወስን ለውሳኔው ዋና ምክንያት በማድረግ በቃለ ጉባኤው ያሰፈረው ምክንያትና ለቦርድ በፃፈው ደብዳቤም የጠቀሰው ምክንያት ድርጅቱ ቀጥታ ለማቅረብ የጠየቀውን ጥያቄ መነሻ በማድረግና የቴክኒክ ኮሚቴ ተዋቅሮ በድርጅቱ የቀረበው ዕቃን እንዲያረጋግጥ ኃላፊነት ተሰጥቶት ባቀረበው የውሳኔ ኃሳብ ብቻ መሆኑንና ምንም አይነት የድርጅቱን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ያልተከተለ መሆኑን መመልከት ተችሏል።

እንዲሁም ተወዳዳሪዎች እንዲጋበዙ ተደርጎ ዝርዝር የሆነ ስፔሲፊኬሽን የተዘጋጀ እና በግልፅ የሚያመለክት መረጃ ማየት ያልተቻለ መሆኑን እንዲሁም ድርጅቱ አሁን አሸናፊ ያደረገውን ድርጅት ያቀረበውን ዋጋ ለማወዳደር የተጠቀመው በገበያ ላይ ያሉ አቅራቢ የሆኑትን ባሻ አህመድ ፕላስቲክና የፕላስቲክ ውጤቶች ማምረቻ (17/03/2016)፣ ቢጂ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል/ማህበር (27/11/2023) እና ሀምቦን ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተ/የግል/ማህበር (27/11/2023) እንዲሁም ጀማል አህመድ ፕላስቲክና የሸራ ውጤቶች መሸጫ (17/03/2016) የሆኑ ድርጅቶች አቅርበውት የነበረውን ዋጋ መሰረት በማድረግ መሆኑ ተመላክቷል።

ድርጅቱ በዚህ መሰረት ዋጋ አወዳደርኩ ይበል እንጂ በገበያ ውስጥ አቅራቢዎች ካሉ ግዥውን በግልፅ ጨረታ በማውጣት በመንግስት የግዥ ስርዓት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተወዳደሪ በመምረጥ ግዥውን መፈጸም ሲገባ ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበውን OMR Import Export የተባለው ድርጅት በመምረጥ ቀጥታ ግዢ መፈፀሙ ሕግና ስርዓትን የጠበቀ ነበር ለማለት አያስችልም። ከዚህ ባሻገር በግዥ ውሉ ላይ የቅድሚያ ክፍያ ብር 5,245,380.00 (አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ አምስት ሺህ ሶስት መቶ ሰማንያ ብር) የግዥ ውል ላይ ይጠቀስ እንጂ አጠቃላይ የግዥ ውል ዋጋው በግልፅ የተመላከተ አይደለም:

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነትና መጠን | የድርጅቶቹ ስም | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ባሻ አህመድ | ቢጂ ትሬዲንግ | ሀምቦን ጠቅላላ ንግድ | ጀማል አህመድ | ሚኪያስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | OMR Import Export |
| | | Unit price | Unit price | Unit price | Unit price | Unit price | Unit price |
| 1. | 9x11strand canvas | 45,540.00 | 45,425.00 | 43,000.00 | 46,000.00 | 45,540.00 | አቅራቢው ያቀረበው የመነሻ የክፍያ ዋጋ ብር 61,600.00 ነው። |
| 2. | 9x11plastic canvas | 14,000.00 | 10,258.00 | 10028.00 | 10,580.00 | 10,350.00 | |

የዕለት ደራሽ ዕርዳታና ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ያካሄደውን ለከባድ መኪኖች ሸራ ግዥ አስቸኳይ ጥናት አስመልክቶ የጥናት ቡድኑ ከጥናት ስራው ማረጋገጥ የቻለው የሸራው ግዥ የመንግስት የግዥ አዋጅ መርሆዎችንና አፈፃፀሞችን እንዲሁም የድርጅቱን ግልፅ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ በተፃረረ መንገድ ግልፅ በሆነ ሁኔታ የተፈፀመ ነው ለማለት አያስችልም።

በዚህም “OMR Import & Export” ብቸኛ አቅራቢ መሆኑንለማረጋገጥ ለሁለት ተቋማት በደብዳቤ ጥያቄ ቀርቦ በተገኘው መረጃ መሰረት፡- የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በፕላስቲክ ሸራ አቅርቦት የተመዘገቡና ህጋዊ ፍቃድ ያላቸው ድርጅቶች ዝርዝር ሲሆን፣ በጥያቄው መሠረት አራት ሺህ የሚሆኑ አቅራቢዎችን ዝርዝር በደብዳቤ አረጋግጦ ልኳል።

**ኮሚቴ ተዋቅሮ በድርጅቱ የቀረበው ዕቃን እንዲያረጋግጥ ኃላፊነት ተሰጥቶት ባቀረበው የውሳኔ ኃሳብ ብቻ መሆኑንና ምንም አይነት የድርጅቱን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ያልተከተለ መሆኑን መመልከት ተችሏል።**

እንዲሁም የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን በደብዳቤ በሰጠው ምላሽ የብቸኛ አቅራቢ ምንነትን አብራርቷል። እንደ ባለስልጣኑ ምላሽ ብቸኛ አቅራቢ ማለት በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 1 ፊደል ሀ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ እና ብቸኛ አቅራቢ ለሚለው ንግድ ፍቃድ ከሚሰጠው አካል በዘርፉ ንግድ ፍቃድ የተሰጠው ለዚህ ድርጅት ብቻ እንደሆነ ሲረጋገጥ መሆኑ በተገለፀው መሠረት “OMR Import & Export” የተባለው ድርጅት ብቸኛ አቅራቢ አለመሆኑን የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከላካቸው ዝርዝሮች ጋር በማገናዘብ ማረጋገጥ ተችሏል።

ከተደረጉ ማጣራቶችና ከተላኩ የደብዳቤ ማረጋገጫዎች በመነሳት የቀድሞ የጥናት ውሳኔ ምክረ ሀሳብን የሚያስቀይር ሆኖ በመገኘቱ ድርጅቱ ብቸኛ አቅራቢ ያልሆነና በሺዎች የሚቆጠሩ በተመሳሳይ ምርት አቅርቦት ግዥ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች መኖራቸውን ተረጋግጧል። ስለሆነም ድርጅቱ ቀጥታ ግዥው እንደዋና ምክንያት የተጠቀመው ብቸኛ አቅራቢ በመሆኑ ነው የሚለው የተሳሳተ የግዥ ሂደት መሆኑን ነው።

ከዚህ ባለፈም አሸናፊ ድርጅቱ ብቸኛ አቅራቢ መሆኑን ከግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዌብ ሳይት በአቅራቢው ተወስዶ በቀረበልን የፅሁፍ ማስረጃ ነው የተባለውን ከተቋሙ የሚመለከተው ባለሙያና ኃላፊ ጋር በስልክ በተደረገው መረጃ ጥያቄ በዌብሳይት ያለው ድርጅቶች በራሳቸው ለመወዳደር የሚጠቀሙበት ማስረጃ እንጂ በተቋሙ የተሰጠ፣ የፀደቀ እና የሚታወቅ አለመሆኑን የተረጋገጠ በመሆኑ ከዌብሳይት ቀረበ የተባለውም ማስረጃ ተገቢ አይደለም።

በመሆኑም ጥናቱ የሚያስረዳው የግዥው ሂደት ግልፅነትን የተከተለ አሰራር ነበር ለማለት የሚያስደፍር አይደለም። ይህ ሁኔታ ባለበት ሁኔታ የግዥው ሂደት እንዲቀጥል ማድረግ የሚቻል አይሆንም። ከዚህ አኳያ የግዥው ሂደት ተቋርጦ አሳታፊ በሆነ መንገድ በግልፅ ጨረታ እንዲፈፀም ማድረግ ይገባል።

ለዚህ ችግር መፈፀም ሚና የነበራቸው ኃላፊዎችና ሰራተኞች እንዲሁም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተሳተፉ አካላት ለጥፋታቸው ተጠያቂ እንዲሆኑ ቢደረግና ድርጅቱ ከዚህ ስህተቱ ታርሞ በቀጣይ ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈፀም የሚመለከታቸው የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች የራሳቸውን የእርምትና የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ምክረ-ሃሳብ ቀርቧል።

# ከሙስና ምርመራ ማህደር

**በዚህ አምድ የተለያዩ ከሙስና እና ብልሹ አሠራር ጋር በተያያዘ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና በሙስና ወንጀል የተመዘበረ የሀገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት እና ግንዛቤ የሚፈጥሩ ዋና ዋና ጉዳዮች አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው።**

የፌደራል ፖሊስ መርማሪ ቀሲስ በላይ መኮንን በአፍሪካ ህብረት ቅጥር ጊቢ ውስጥ በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ውስጥ በአካል ቀርበው ሀሰተኛ የክፍያ ሰነዶችን በመያዝ ለ3 ግለሰቦች እና ለአንድ የግል ድርጅት ሒሳብ 6 ሚሊየን 50 ሺህ ዶላር ሊያዘዋውሩ ሲሉ በአፍሪካ ህብረት ሴኪዩሪቲዎች ተይዘው ለፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ተላልፈው መሰጠታቸውን ጠቅሶ የጥርጣሬ መነሻውን ለችሎቱ አቅርቧል።

ተጠርጣሪ ቀሲስ በላይ መኮንን ድርጊቱ መፈጸሙን አምነው፤ ይሁን እንጂ ወንጀል አለመፈጸማቸውን አስረድተዋል። ስለሆነም የዋስትና መብታቸው እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል። የግራ ቀኝ ክርክሩን የተመለከተው ጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ ተጠርጣሪው ያቀረቡትን የዋስትና ጥያቄ በማለፍ ለፖሊስ የምርመራ ማጣሪያ ጊዜ ፈቅዷል።

መርማሪ ፖሊስ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ የምስክሮችን ቃል መቀበሉን፣ በተጠርጣሪዎች እጅ ላይ የተገኘ ኤሌክትሮኒክስ ምርመራ እንዲደረግ ለሚመለከተው ተቋም መጠየቁን፣ የቴክኒክ ምርመራ እንዲሰጠው በደብዳቤ መጠየቁን፣ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ለአፍሪካ ህብረት የሰነድ ማስረጃዎች እንዲሰጠው መጠየቁን፣ ተጠርጣሪዎቹ በስማቸው የሚገኙ ሂሳቦችን ለማጣራት ማረጋገጫ እንዲሰጠው በደብዳቤ መጠየቁን፣ በወቅቱ የነበረ የካሜራ ቅጂ መጠየቁን፣ ለወንጀል ተግባር የዋለ ተሽከርካሪ ማረጋገጫ ከሚመለከተው ተቋም መጠየቁን፣ በቀሲስ በላይ ሁለት መኖሪያ ቤቶች ላይ ብርበራ ማድረጉንና በብርበራ የተገኘ የጦር መሳሪያ ህጋዊነት የማረጋገጥ ስራ እየሰራ መሆኑን በመጀመሪያው ቀጠሮ ገልጿል።

በሁለተኛው ቀጠሮ ተጠርጣሪው ቀሲስ በላይ መኮንንን ጨምሮ ሌሎቹም ተጠርጣሪዎች በ6 ጠበቆች ተወክለው ችሎት የቀረቡ ሲሆን÷ ጠበቆቻቸው ፖሊስ ያቀረበው ጊዜ ቀጠሮ መጠየቂያ ምክንያቶች ደንበኞቻቸውን ተጨማሪ በእስር ለማቆየት የሚያስችል አይደለም በማለት ተከራክረዋል። በደንበኞቻቸው ቀሲስ በላይ የተገኘው የጦር መሳሪያ ህጋዊ መሆኑን በመጥቀስ ሀብት ማፍራት ከተጠረጠሩበት ወንጀል ጋር ሊገናኝ አይገባም በማለት የመከራከሪያ ነጥብ አንስተዋል። የሃይማኖት አባት መሆናቸውን፣ የልማት ስራ አስተባባሪ በመሆናቸውና ቋሚ አድራሻ እንዳላቸው በመጥቀስ ቢወጡ ከመንግስት ተቋማት የሚመጡ ማስረጃዎችን የማጥፋት አቅም የላቸውም በማለት የዋስትና መብታቸው እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል።

ቀሲስ በላይ በበኩላቸው÷ ወንጀል አለመፈጸማቸውን ገልጸው፤ ለሀገር እና ለፖሊስ ተባባሪ መሆናቸውን እንዲሁም ምሽት ላይ እቤቴ እየሄድኩ ጠዋት ልምጣላችሁ በማለት ፖሊስን መጠየቃቸውን ለችሎቱ አስረድተዋል። አብረዋቸው የታሰሩት ሹፌራቸውና አጃቢያቸው መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ምንም የወንጀል ተሳትፎ በሌለበት ሁኔታ ላይ ከኔ ጋር ተጨማሪ ጊዜ በእስር ማቆየት ተገቢ አይደለም በማለት የዋስትና መብታቸው እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል። የመርማሪ ፖሊስ በጠበቆች ለተነሱ መከራከሪያ ነጥቦች ላይ መልስ የሰጠ ሲሆን÷ በዚህም ምርመራው ተጠናቋል ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጥ አይገባም ለሚለው የጠበቆች መከራከሪያ በሚመለከት ፖሊስ ሰፊ ምርመራ ስራ እንደሚቀረው ግብረአበሮችንም የመያዝ ስራ ገና እየተሰራ መሆኑን ገልጿል።

ከዚህ በፊት ተመሳሳይ ተግባሮች መኖራቸውን ጠቅሶ፤ በተደረገ ብርበራ ተጨማሪ ማስረጃ ማግኘቱንና ማስረጃውን ተከትሎ ምርመራውን እያሰፋ እንደሚያጣራ ተናግሯል። በተጨማሪም ተጠርጣሪዎቹ ቢወጡ ማስረጃ ሊሰወር ይችላል በማለትም የዋስትና ጥያቄያቸውን ተቃውመዋል። የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ህግ በመዝገቡ ላይ ተሰይሞ የምርመራ መዝገቡ መረከቡን ጠቅሶ፥ ተመልክቶ ለመወሰን እንዲያስችለው በወ/መስ/ህ/ቁጥር 109/1 መሰረት የ15 ቀን ክስ መመስረቻ ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቋል። በተጨማሪም ዐቃቤ ህግ የተጠረጠሩበት ወንጀል ድርጊት ሀሰተኛ ሰነድ መገልገልና ንግድ ባንክን ማታለል መሆኑን ጠቅሶ፥ በሙስና አዋጁ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 እና አንቀጽ 32 ስር ሊያስከስሳቸው እንደሚችል ገልጿል።

ተጠርጣሪዎቹ ከ6 ሚሊየን ዶላር በላይ ጥቅም ሊገኝበት እንደነበር ከ10 ዓመት በላይ በሚያስቀጣ ድንጋጌ ሊያስከስሳቸው እንደሚችል ተናግሮ የጠየቀው ዐቃቤ ህግ፥ የ15 ቀን የክስ መመስረቻ እንዲፈቀድለት ጠይቋል። የተጠርጣሪ ጠበቆች በበኩላቸው፥ በፖሊስ ሲከናወን የቆየው ምርመራን የሚመራው ዐቃቤ ህግ መሆኑን ጠቅሰው እንደ አዲስ መዝገቡን ተመልክቼ ለመወሰን 15 ቀን ክስ መመስረቻ ይሰጠኝ ማለቱ ተገቢ አይደለም በማለት የዐቃቤ ህግ ክስ መመስረቻ ጊዜ ጥያቄውን በመቃወም ተከራክረዋል።

ጠበቆቻቸው ክስ ባልተመሰረተበት ሁኔታ ላይ ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ ይችላል ተብሎ በግምት ሊገለጽ አይገባም በማለት ተከራክረዋል። ሰነዱ የቀረበው ለውጭ ሀገር ድርጅት ሂሳብ በመሆኑ በፀረ-ሙስና አዋጅ ሊታይ እንደማይችል በመግለጽ በሙስና ሊከሰሱ ይችላሉ ተብሎ በዐቃቤ ህግ መገለጹ አግባብ አይደለም በማለት ተከራክረዋል። በተጨማሪም ጠበቆቹ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠርጣሪዎች ላይ ምንም ተሳትፎ ባልተገለጸበት ሁኔታ ላይ አብረው በእስር መቆየታቸው እና ክስ መመስረቻ ጥያቄ መቅረቡን ተቃውመዋል። ጠበቆቹ "ሰነዱ የቀሲስ በላይ ስም ሆነ ሌሎች ተጠርጣሪዎችን ስም ባልጠቀሰበት ሁኔታ ላይ ቅንነት በጎደለው መልኩ ወንጀል ተብሎ መቅረቡ አግባብ አይደለም" በማለት ጠበቆቹ መከራከሪያ ነጥብ አንስተዋል።

በጠበቆች በኩል ቅንነት የጎደለው ተግባር ነው ተብሎ በተገለጸው ክርክርን በሚመለከት ስነስርዓታዊ አለመሆኑን በመጥቀስ ዐቃቤ ህግም ሆነ ተቋሙ ማንንም ለመጉዳት እንደማይሰራና ህግን ተከትሎ የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ ስራ ብቻ እንደሚሰራ አብራርቷል። የውጭ ሀገር ሂሳብና ሰነድ በኢትዮጺያ ፀረሙስና አዋጁ ሊታይ የማይችል መሆኑን ጠበቆች የጠቀሱበትን ነጥብ በሚመለከት መልስ የሰጠው ዐቃቤ ህግ የማታለል ተግባር ሊፈጸም የነበረው ህጋዊ ሰውነት ባለው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መሆኑን ጠቅሶ ÷ ክፍያው ተፈጽሞ ቢሆንና ጉዳት ቢደርስ ተጎጂው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መሆኑን ጠቅሶ፤ መታየት ያለበት በሙስና አዋጁ 881 /2007 ስር ነው በማለት በመከራከር መልስ ሰጥቷል።

ሰነዱን በሚመለከት ደግሞ ሰነዱ ንግድ ባንክ ቀርቦ የነበረ መሆኑን በመጥቀስ በህዝባዊ ድርጅት ወይም በመንግስታዊ ድርጅት ስር የሚታይ ሰነድ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 23/3 ስር ይካተታል በማለት ተከራክሯል። ወንጀል በሌለበት ወንጀል ተብሎ ሊቀርብ አይገባም በማለት ለቀረበ የጠበቆች መከራከሪያን በሚመለከት ደግሞ ዐቃቤ ህግ በወንጀል ህጉ ሞራላዊ፣ ህጋዊና ግዙፋዊ ጉዳዮችን ያሟላ የወንጀል ድርጊት መሆኑን ገልጾ፥ በሙስና አዋጁ እንደሚካተትና ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ በሚችል ድንጋጌ ስር ሊያስከስስ እንደሚችል ጠቅሶ መልስ ሰጥቷል።

2ኛ እና 3ኛ ተጠርጣሪዎች ምንም ተሳትፎ የላቸውም በተባለው ጉዳይ ላይ ዐቃቤ ህግ ግብረዓበር ናቸው በማለት በአዋጁ ከአንቀፅ 32 እስከ አንቀጽ 37 ድረስ ባለ ድንጋጌ ስር በግብረአበርነት ክስ ሊቀርብባቸው እንደሚችል ገልጾ ማብራሪያ ሰጥቷል። የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረው ጊዜ ቀጠሮ ችሎት ግለሰቦቹ የተጠረጠሩበት ወንጀል በሙስና አዋጁ ስር የሚታይና ዋስትና የሚያስከለክል መሆኑን ጠቅሶ፥ ተጠርጣሪዎቹ ክስ እስኪመሰረትባቸው ባሉበት ማረፊያ ቤት እንዲቆዩ በማለት ዐቃቤ ህግ የጠየቀውን የ15 ቀን ክስ መመስረቻ ጊዜ ፈቅዷል።

ወደ ገጽ 22 ዞሯል..

# ኪነ-ጥበብ

## የእጅ አመል

ቢኖረን ቢተርፈን ኪሳችን ቢሞላ፣
ብንሰጥ ብናበድር ብንተርፍ ለሌላ፣
ብንደግስ ብናቀርብ ህዝብ ብናበላ፣
ሰርቀን ባመጣነው ህዝብ ብናታልል፣
በስውር ወስደነው ጥሩ መሳይ ሆነን..
ለህዝብ ብናስመስል፤
ለጊዜው ነው እንጅ አየድግ አይቀጥል
አመል ሆኖን እንጅ...
ብዙ ነው መዘዙ ወደ'ኒላ ሚጥል፡፡
ጊዜው ብዙ ሆኗል ስራው ከሸመነ፣
ስሩን ከሰደደ ስሙን ካገነነ፣
ውሸት ከተካነ፣
እውነት ካመነነ፣
ቆይቷል ሙስና የእጅ አመል ከሆነ፣
ቆይቷል ሙስና የእጅ አመል ከሆነ፡፡
ሙስና ዛሬ ላይ፣
የእጅ አመል ሆኖብን፣
የህዝቡን ላብ ንብረት፣ ምን ብንመዘብርም፣
ሙስናን ወንጀል አካብተን ብንቃርም፣
በዘረፍነው ንብረት ቤት ሰርተን ብንኖርም፣
የህዝብን ገንዘብ ለግል ብናደርግም፣
በመጨረሻ ግን መመለሱ አይቀርም፣
ዛሬ ያለ ቢመስል ነገ አብሮን አይኖርም፡፡

በያብባል አዲስ

# መልካም ዜና

## በዓለማየሁ ማሞ

‹‹ፍትሕ ለሁሉም›› የሚል ጽኑ አቋም ስላለው ከልጅነቱ ጀምሮ የሕግ ትምህርት የማጥናት ህልም ነበረው:: ህልሙ ዕውን ሆኖ ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በሕግ የትምህርት ዘርፍ በማዕረግ የመጀመርያ ዲግሪውን አግኝቷል:: ነገር ግን ገና ከጅማሬው የሕግ ትምህርቱን ሲጀምር የቅርብ ወዳጅ ዘመዶቹ ‹‹ሙሰኛ እና ሌባ›› እየበዛ ባለበት አገር፣ ፍትሕ በሌለበት አገር ለምን ለፍትሕ ስትል ዋጋ ትከፍላለህ ሲሉ ተቃውመውት ነበር::

እርሱ ግን ‹‹ከፍትሕ ጋር ቆሜ የሚመጣውን እቀበላለሁ›› በሚል የዓላማ ፅናት የሕግ ትምህርቱን በማዕረግ ካጠናቀቀ በኋላ የጠበቃነት ሥራውን በሀዋሳ ከተማ ጀመረ:: በሥራው ላይ እያለ ለፍትሕ ሲዋደቅ አንድ ግለሰብ ባደረሰበት ጥቃትና ጥቃቱን ተከትሎ ባጋጠመው ከባድ ጉዳት ዛሬ ላይ የሕግ ባለሙያውና ደራሲው ዳግማዊ አሰፋ ከአንገቱ በታች ያለውን ሙሉ የሰውነት ክፍሉን መቆጣጠርም ሆነ ማዘዝ ተስኖት ዊልቸር ላይ ተቀምጦ መዋል ከጀመረ ዓመታት ነጉደዋል::

ዳግማዊ በደረሰበት ጥቃት እጆቹ ተሳስረው መያዝ መጨበጥ ቢሳናቸውም፣ እግሮቹ ቄጠማ ሆነው መራመድ ተስኗቸው ዊልቸር ላይ ቢውሉም፣ የተኛበትን ጎኑን በራሱ ተገላብጦ ለመቀየር ቢሳነውም፣ ማንኛውንም እንቅስቃሴ ከሰው ዕርዳታ ውጭ የማድረግ አቅም ባይኖረውም፣ አካሉ ዊልቸር ላይ ተቀምጦ እጆቹ ብዕር መጨበጥ ባይችሉም አዕምሮው ግን በይቅርታ ነፃ ወጥቶ እጅግ ርቆ እየተጓዘ ነው:: የፅናትም ተምሳሌት ነው:: የዳግማዊን የይቅርታ ሐሳብና ምክር ‹‹ምክርና ቡጢ ለሰጪው ቀላል ነው›› ብሎ ማራከስና ማቃለል አይቻልም ይለናል ፀሐፊና ገጣሚ አንዱዓለም አባተ (የአፀደ ልጅ) ታሪኩን በጥልቀት ተመልክቶ በመጽሐፉ ሽፋን ላይ በሰጠው አስተያየት:: ከእርሱ ባላነሰ አብረው ታመውና ተጎድተው፣ የመከራ ጽዋና ለቁጥር የሚታክቱ ውጣ ውረዶች ተጋርተው ለዚህ ያበቁትን ወገኖቹን ተስፋ ለማለምለምና መልዕክቶቹን ለታዳሚው ለማድረስ የሄደበትን ርቀት፣ የነበረውን የዓላማ ፅናትና ትጋት በአዲስ ሕይወትና ከማዕዘኑ ወዲህ በተሰኙ ድርሰቶቹ ውስጥ እንመለከታለን::ዳግማዊ ‹‹አዲስ ሕይወት›› በሚል ርዕስ ያዘጋጀው የመጀመርያው መጽሐፍ በ142 ገጾች የተቀነበበ ፈተና፣ የማሸነፍ ትግል፣ መቀበል፣ ዕይታን፣ ተስፋና አዲስ ሕይወት በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ለአንባቢዎች የሕይወት ልምዱን አካፍሏል:: በአንድ ወቅት ከካይሮፕራክተር ሰላምአክሊሉ(ዶ/ር) ጋር በነበረው ቆይታ ስለሰጠችው መሠረታዊ ምክር አመስግኖ፣ ያቀረበችለትን ፈታኝ ጥያቄ እንዲህ ሲል በአዲስ ሕይወት መጽሐፉ አጋርቶናል:: ዳግማዊ ‹‹አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ?›› ትለዋለች ዶክተር ሰላም:: ዶክተሯም ለጥያቄዎ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኑን ካረጋገጠች በኋላ ‹‹ይህንን ጉዳት ያደረሰብህን ሰው ይቅር ልትለው ትችላለህ?››፣‹‹ይቅርታ የማድረግ አቅሙ አለህ?›› የሚል ጥያቄ አንስታለት ነበር::

ምላሹ በቀላሉ የሚሰጥ በቃል ብቻ የሚገለጽ ሳይሆን ልባዊ ስሜትንና ተግባርን ማዋሃድ የሚጠይቅ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፣ ብዙ ፈትኖኛል! ተምሬበታለሁ ይላል ዳግማዊ በመጽሐፉ:: ‹‹ከዚህ በኋላ እኔ ላይ ለሆነው ነገር በሙሉ ምንም ዓይነት የበቀል ሥፍራ የለኝም:: በዚህም ትልቁን ሸክም ከራሴ ላይ አውርጄዋለሁ:: ሕይወት ትቀጥላለች ዛሬን ከጥላቻ ነፃሆኜ እየኖርኩ ነገን በብሩህ ተስፋ እጠብቃለሁ:: ሁልጊዜም የተሻለውን ቀን በአዕምሮዬ እየቀረፅኩና እያየሁ ለህልሜ ዕውን መሆን እተጋለሁ፤›› ሲል በመጽሐፉ አስፍሯል:: ዳግማዊ አሰፋ ሁለተኛውን መድበል ይዞ ከተፍ ብሏል::

‹‹ከማዕዘኑ ወዲህ›› በሚል ርዕስ በእውነተኛ ታሪክ ላይ ለተመሠረተው መጽሐፉ የሰጠውን ርዕስ ዳግማዊ ሲያብራራ፣ ‹‹ማዕዘን መታጠፊያ ነው:: የአንድ መስመር ማክተሚያና የሌላ መስመር ማስጀመርያ ነው:: ማዕዘን የመዞሪያ ነጥብ ነው:: ነጥቡ ደግሞ የሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎች መጋጠሚያ ነው:: የአንድ ጎዳና ማክተሚያና የሌላ ጎዳና መጀመርያ፣ ከአንድ መስመር ተለይቶ ወደ ሌላ አቅጣጫ መታጠፊያ፣ የጠቢቡ ሰሎሞንን ምሳሌ በመጠቀምም ከአዳዲስ ነገሮችና የሕይወት ገጠመኞች ጋር ራሳችንን ከማላመድ አኳያ ወጣትነት በእርጅና ጣጣዎች ይተካል፤››‹‹ጥንካሬ ለድክመት፣ ፍጥነት ለዝግመት፣ ብርሃን ለጨለማ፣ ማውራት ለዝምታ፣ ዕርምጃ ለመኝታ፣ መከበብ ለብቸኝነትና ማግኘት ለማጣት ወዘተ. ቦታቸውን የሚለቁበት የእጥፋት ቦታ ወይም ማዕዘን አለ:: ከዚህ የእጥፋት ነጥብ ወዲህ ያለውን ጎዳና የማዕዘኑ ወዲህ ብየዋለሁ፤›› ይለናል:: ‹‹ይቅርታ ቂምን ሽሮ ፍቅርን ያነግሣል:: በቀልን ሽሮ ሕይወትን ያሰፍናል፣ የተበዳይን ልብ አራርቶ የበዳይን በደል ይፍቃል፣ እውነተኛ ይቅርታ የአሮጌ ሕይወትን እርሾ አጥፍቶ ለአዲስ ሕይወት ጅማሮ መሠረት ነው፤›› በሚል በጥቅሉ ከዳግማዊ አንደበት ሁሌም የማይለየውን ‹‹ይቅር ባይ ልብና ምሕረት የሚሰጥ ህሊና ቢኖረን ከማንም ቀድመን የምንጠቀመው እኛ እንጂ የበደለን ሰው አይደለም::

በልባችን የቋጠርነውን ቂምና በቀል ፈቅደን ትተን ይቅር ብንል የህሊና ዕረፍት፣ የመንፈስ ሰላምና ዕርካታ የምናገኘው እኛው ራሳችን ነን፥ ይቅር የምንለው ለራሳችን ብለን ነው፤›› የሚለውን ምክር አዘል መልዕክት አስተማሪ ሆኖ አግኝተነዋል::መጋቤ ሐዲስ እሸቱ ዓለማየሁ በዚህ መጽሓፉ ሽፋን ገጽ ላይ በሰጡት አስተያየት፣ ‹‹ጸሐፊው በሁለተኛ መጽሐፍ በመምጣቱ ደስታ ተሰምቶኛል:: ከዚህ መጽሐፍ ሁለት ነገሮችን አግኝቼበታለሁ:: ፅናትናይቅርታ!›› ይሉናል:: ጸሐፊው ያን ያህል ግፍና በደል ተፈጽሞበት ቂምና ጥላቻን ትቶ ይቅርታ ማድረጉ በእጅጉ እንዳደንቀውና እንድማርበት አድርጎኛል:: አካሉ ዊልቸር ላይ ተቀምጦ እጆቹ ብዕር መጨበጥ ባይችሉም አዕምሮው ግን በይቅርታ ነፃ ወጥቶ እጅግ ርቆ እየተጓዘ ነው::የፅናትም ተምሳሌት ነው:: መጽሐፉን ሁሉም ሰው እንዲያነበው እጋብዛለሁ:: ዳግማዊም ደጋግሞ እንዲጽፍ አደራ እላለሁ፤›› ሲሉ ልበ ብርሃኑ መጋቤ ሐዲስ እሸቱ መስክረዋል::የመጋቤ ሐዲስን አስተያየት በማጠናከር ወጣት ዳግማዊ አሰፋ አቦሉን — በአዲስ ሕይወት፣ ወለላውን — ከማዕዘኑ ወዲህ እንዳጋራን ሁሉ በበረካውና በሦስተኛው ሥራው እንደምንገናኝ አምናለሁ::

---

ከ ገጽ 20 የዞረ..

## ቀሲስ በላይ መኮንን...

ከዚህ የማጭበርበር የሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የአፍሪካ ህብረት በፈረንጆቹ ሚያዝያ 15 ቀን 2024 በዋና መስሪያ ቤቱ ከሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሀሰተኛ ሰነድ ገንዘብ ለማዛወር የተደረገውን ሙከራ አውግዟል::

ጉዳዩን አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሰራተኞች እና የህብረቱ የፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ምንም ገንዘብ እንዳይወጣ በማድረግ የተቃጣውን የማጭበርበር ሙከራ ለማክሸፍ ለወሰዱት ፈጣን እርምጃም አድናቆቱን ገልጿል:: በወቅቱ የተፈጠረው ክስተትም የአፍሪካ ህብረት ተቀጣሪ ባልሆነ ግለሰብ በአፍሪካ ህብረት ዋና መሥሪያ ቤት ውስጥ በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ሀሰተኛ የክፍያ ማዘዋወሪያ ትዕዛዝ መቅረቡን አመላክቷል::

ህብረቱ እንደገለፀው፤ የክፍያ ማዘዋወሪያ ትዕዛዞቹም በግንባታ እና የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራዎች ስር ለተለያዩ አካላት የሚከፈል ከ6 ሚሊየን ዶላር በላይ የሆነ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቁ ነበር:: ይሁንና የህብረቱ የፋይናንስ ዳይሬክቶሬት በሰነዶቹ ላይ ባደረገው ጥንቃቄ የተሞላበት ምርመራ ሰነዶቹ ሀሰተኛ ሆነው በመገኘታቸው ምንም ዓይነት ገንዘብ እንዳይወጣ በመደረጉ ህብረቱን ከኪሳራ መታደግ እንደተቻለ አመላክቷል:: መረጃ የደረሳቸው የኢትዮጵያ የፀጥታ ኃላፊዎችም ግለሰቡንና በማጭበርበር ተግባሩ የተሳታፉ ተባባሪዎቹን አስፈላጊውን የምርመራ ሂደት ለማከናወን በቁጥጥር ስር ማዋላቸውን ነው የጠቀሰው::

የተቃጣውን የማጭበርበር ሙከራ በፅኑ ያወገዘው የአፍሪካ ህብረት፤ ጉዳዩን በከፍተኛ ትኩረት እየተከታተለው መሆኑንም ነው በመግለጫው ያመላከተው:: የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና የኢትዮጵያ መንግስት በወቅቱ በመድረስ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረጋቸውም የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ምስጋና አቅርቧል::